# ሐመር

# “እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ”




## በውስጥ ገጾች


- ✞ መርከባችን ወደቡ ላይ እንድትደርስ  ሁላችንም የቀዛፊነትን ድርሻ እንወጣ።
- ✞ ስለዚያችም ምድር ክፉ የተናገሩ ሞቱ
- ✞ “እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ”
- ✞ አቡነ ዮሐንስ ዘውራ ኢየሱስ
- ✞ “መልካም ማድረግን አትርሱ”
- ✞ የፍስክ ብፌ
- ✞ አሐቲ ቤተ ክርስቲያን



ሚያዝያ ፳፻፲፫ ዓ.ም.

# ሐመር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣
ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት
ጠብቆ የሚወጣ

## ሚያዚያ ፳፻፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመትና
ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ዋና ክፍል
በመጽሔት ዝግጅት ክፍል የሚዘጋጅ
ትምህርታዊ መጽሔት



## ማውጫ

**የማኅበሩ መልእክት**
መርከባችን ወደቡ ላይ እንድትደርስ ሁላችንም የቀዛፊነትን ድርሻ እንወጣ፡፡ ፫

**ዐውደ ስብከት**
ስለዚያችም ምድር ክፉ የተናገሩ ሞቱ ፭

**ትምህርተ ሃይማኖት**
"እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ" ፲

**እናስተዋውቃችሁ**
አቡነ ዮሐንስ ዘውራ ኢየሱስ ፲፭

**የጥያቄዎቻችሁ መልስ** ፲፰

**ክርስትና በማኅበራዊ ሕይወት**
"መልካም ማድረግን አትርሱ" ፳፬

**ኪነ ጥበብ**
የፍስክ ብፌ ፳፰

**የነገዋ ቤተ ክርስቲያን**
አሐቲ ቤተ ክርስቲያን ፴፩

፴ማኅበረ ቅዱሳን፴ እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይኽን ስያሜ አግኝቷል፡፡

## የዝግጅት ክፍሉ

ስልክ ፲፩፩-፰-፩፪-፪፰-፬፱
ፖ.ሣ.ቁ ፰፲፲፯፰
ኢ-ሜይል magazine@eotcmk.org
የማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት ስልክ
፲፩፩-፩-፭፭-፫፪-፫፱
የልማት ተቋም የስርጭት ክፍል ስልክ
፲፩፩-፩-፪፫፬፭-፪፱
የማስታወቂያ ዝግጅት ክፍል ስልክ
፲፱፬፪-፫፰-፩፯-፱፩

**ም/ዋና አዘጋጆች**
ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ
አድራሻ፡- ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ
ወረዳ ፲፭ የቤት ቁ. ፯፪፲

**ምክትል ዋና አዘጋጅ**
ዲ/ን ኅሊና በለጠ

**ከፍተኛ ሪፖርተር**
ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን

**ሌይ አውት ዲዛይነር**
ግደይ ገብሬ

**ጸሓፊ**
ገነት ታደሰ

# መርከባችን ወደቡ ላይ እንድትደርስ ሁላችንም የቀዛፊነትን ድርሻ እንወጣ።

## የማኅበሩ መልእክት

ለዘመናት መንገደኞቿን አሳፍራ እግዚአብሔር አምላክ ወዳዘጋጀላቸውና ተስፋ ወደሚያደርጉት ወደብ ስታደርስ የኖረችው መርከብ (ቤተ ክርስቲያን) በፈተና ውስጥ ያላለፈችበት ጊዜ ነበር ባይባልም ዛሬ ዛሬ ግን ከሌላው ጊዜ በተለየና በከፋ ሁኔታ ማዕበሉ እየናጣት ትገኛለች። እንደሚታወቀው ይቺ መርከብ ጉዞዋ በባሕር ላይ ነው። ባሕሩ ደግሞ በታላቅ ሞገድ የሚናወጽ ማዕበል ያለበት በመሆኑ ጠንካራና ባለሙያ ቀዛፊ ካልያዛት ከነተሳፋሪዎቿ ልትሰጥም ትችላለች። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ያለ ቅጣት ብትኖሩ ዲቃሎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም። (ዕብ. ፲፪፥፰) በማለት እንደተናገረው ምንም እንኳን ከቅጣትና ከተጋድሎ በኋላ ዘለዓለማዊ ክብር የሚገኝ ቢሆንም ይህን የቅጣትና የተጋድሎ ማዕበል ግን በትዕግሥት ማለፍን ይጠይቃል። መርከባችን በባሕሩ ላይ ያለውን ጽኑ ማዕበል ተቋቁማ ባሕሩን ከተሻገረች በኋላ ከገቡ የማይወጡበትን ካገኙ የማያጡትን ወደብ (መንግሥተ ሰማያት) ትወርሳለች። ይሁን እንጂ እንደዚህ ካለው ወደብ ላይ ለመድረስ በባሕሩ ውስጥ ያለውን ማዕበል ማለፍ ይጠይቃል።

መርከባችን የምትናጥበት ማዕበል የእርስ በእርስ ጦርነት፣ የዓለም ጠበብቶች መድኃኒት ያላገኙለት በሽታ፣ አርሶ አደሮቹ ዓመቱን ሙሉ ሲለፉበት የከረሙበትን ሰብል አንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ የሚያወድም የአንበጣ መንጋ፣ ጊዜውን ባልጠበቀ ዝናም የሚከሠት የጎርፍ አደጋ፣ በመርከቢቱ ውስጥ ሥር የሰደደውና መፍትሔ ያልተበጀለት የእርስ በእርስ ክፍፍል ወዘተ. ሁሉ እጅግ የመከራ ጊዜዋን እያራዘመና የመስጠም ዕድሏን እያሰፋው ይገኛል። ስለዚህ ምእመናን የተሳፈሩባት ይህቺ መርከብ ይህን ሁሉ ተግዳሮት አልፋ ተሳፋሪዎቿንም ወደ አሰቡትና ተስፋ ወደሚያደርጉት ወደብ ለማድረስ ሁሉም እንደየድርሻው መሳተፍ ይኖርበታል።

ምድራዊ ባሕርን ለመሻገር መርከብ ውስጥ ለሚሳፈሩ ሰዎች ምን አልባት የተሳፋሪነት ሕጉ የተወሰነ ሊሆን ይችላል። ይህም ለቀዛፊው ዋጋ ከመክፈል ያላለፈ ሊሆን ይችላል። ወደ ማያልፈውና ወደ ዘለዓለማዊው ወደብ ታደርሳቸው ዘንድ ምእመናን የተሳፈሩባት መርከብ ግን ለሁሉም ድርሻ ሰጥታ እንደተሳፋሪ ብቻ ሳይሆን እንደቀዛፊ እንዲያስቡ፣ ከማሰብም በላይ የየድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ታስተምራለች። ድርሻቸውን የሚወጡበት አጋጣሚ ደግሞ አስቀድመው በመርከቧ ውስጥ ገብተው ከመሳፈር የሚጀምር ሲሆን በመርከቧ ውስጥ ያለውንና የሌለውን ለይቶ ማወቅንም የሚያጠቃልል ነው።

ለዚች መርከብ መሻገርና ከወደቡ ላይ ለመድረስ አባቶች የአባትነት ድርሻቸውን በመወጣት ማለትም፡- ወጣቱን በመምከር፣ ፊት አይተው ሳያዳሉ ጥፋተኛውን በመገሠጽ፣ ሀገር ሰላም እንድትሆን ዕለት ዕለት ስለ ሰላም በመጸለይ፣ የውስጥ ክፍፍሉንም በምክክርም፣ በጸሎትም፣ የአበውን የችግር አፈታት ዘዴ በመጠቀም ሊፈቱት ይገባል። እንደ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር ያለውን ክፍፍልም ቁርጠኝነት በተሞላበት መንገድ በመመልከት ምክር የሚያስፈልገውን በመምከር፣ ተግሣጽ የሚገባውን ጽኑ ማዕበል የሆነውን የትውልዱን ክፉ ሐሳብም በመገሠጽ መርከቧን ዳር የማድረስ የራሳቸውን የቀዛፊነት ድርሻ ሊወጡ ይገባል።

በዚቺ መርከብ ውስጥ የተሳፈሩት አባቶች ብቻ አይደሉም፡፡ መንፈሳዊ ማኅበራትም ይገኙባታል፡፡ እነዚህ ማኅበራት የዚች መርከብ በባሕር ውስጥ መስጠም የሚያደርሰው አደጋ እነርሱንም አብረው እንዲሰጥሙ የሚያደርግ ነውና እንዳትሰጥም ለማድረግ ከአባቶቻቸው ጋር በመሆን አብሮ መታገል ይኖርባቸዋል፡፡ ከእግራቸውም ሥር ሆነው የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ መሠረት ያደረገ ምክራቸውን ከልብ በማዳመጥ ምእመናን የተሳፈሩባትን መርከብ ከስጥመት ሊታደጓት ይገባል፡፡

መንግሥትም እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን የተሳፈሩባት መርከብ ከሰጠመች እርሱም አብሮ የሚሰጥም መሆኑን ከወዲሁ ሊገነዘብ ይገባል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ምእመናን በሃይማኖታቸው (በክርስትናቸው) የክርስቶስ ዜጎች ቢሆኑም እንደ ሀገር ሲታዩ ኢትዮጵያውያን ናቸውና፡፡ ሕዝቡ ከመርከብ ጋር አብረው ከሰጠሙ የሚመራው ሕዝብ የሌለው መንግሥት ወይም ሕዝብ አልባ መንግሥት ሊሆን ስለሚችል ነው፡፡

ምእመናን የተሳፈሩባትን መርከብ ከስጥመት ከመታደግ አኳያ ድርሻ ካላቸው አካላት መካከል ወጣቱ ይገኝበታል፡፡ ሀገር በሰላማዊ መንገድ እንጂ በጦርነት አትገነባም፤ ወደ ጦርነት የገቡ ሀገራት ሲፈርሱና ሲበታተኑ እንጂ ሲያድጉ፣ ሲገነቡ፣ ሲበለጽጉ አልታዩምና ከጊዜያዊ ስሜት ወጣ ብሎ በሰላማዊ መንገድ መወያየትና የሚቀርበውን ጥያቄም በአግባቡ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ ወደ ፊት እየታሰበ ያለውን ሀገራዊ ምርጫም በሰላማዊ መንገድ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ ሊነሡ የሚችሉ ጥያቄዎችም ካሉ ከዚያ በኋላ ማንሣት የሚገባ መሆኑን ልብ ሊለው ይገባል፡፡ ለቤተ ክርስቲያንም ብሎም ለሀገር የሚገባውን ጉዳይ በሰከነና በተረጋጋ መንፈስ ሆኖ ዘላቂ መፍትሔ ለማምጣት መታገል ግድ ይላል፡፡

በብሔር፣ በዘር፣ በጎሣ፣ በሃይማኖት ወዘተ ሳንከፋፈል ምእመናን የተሳፈሩባትን መርከብ ከስጥመት ልንታደጋት ይገባል፡፡ የአንዱ ጉዳት ለሌላው ሊታየው፣ የአንዱ ሕመም ሌላውንም ሊያመው ይገባል፡፡ ምክንያቱም በጎረቤት የሚነድ እሳት የጎረቤቴን ቤት ነው የሚያቃጥለውና ችግር የለውም ብለን ዝም የምንል ከሆነ ወደ እኛ ቤት መድረሱ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ችግሩን የሁላችንም አድርገነው በመረባረብ ልንታደጋት ይገባል እንጂ ጉዳት የደረሰበት የአንድ ወገን ቤተ እምነት፣ ብሔር፣ ጎሣ ወዘተ. ብቻ መጮህ የለበትም፡፡

ለመስማትም፣ ለማየትም በሚከብድ ጽኑ ማዕበል እየተናጠች ያለችው ነገር ግን በርካታ ተሳፋሪዎችን ያሳፈረችው መርከብ ካለባት ተግዳሮት ወጥታ ወደሰላማዊው ወደብ ትደርስ ዘንድ በውስጧ ከተሳፈሩት መንገደኞቿ ባሻገር ከውጭ ሆነው የሚመለከቷትም ለደኅንነቷ ሊረባረቡ ይገባል፡፡ ቀዛፊዋም እንደዚሁ መርከቢቱና መንገደኞቿ በባሕር ሰጥመው እንዳይቀሩ የራሱን የቀዛፊነት ድርሻ በንቃት ሊወጣና ተሳፋሪዎችን ሊደርሱ ካሰቡበት ወደብ ሊያደርሳቸው ይገባል፡፡ ተሳፋሪዎችም እንዲህ ያለውን የቀዛፊነት ድርሻ ሊረባረቡበት እንደሚገባ መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ ትብብርና የአንድነት ጉዞ ውስጥ ደግሞ ጎልቶ የሚታይ ድርሻ ካለው አካል ጀምሮ ሁሉም ድርሻ እንዳለው መዘንጋት የለበትም፡፡ ስለዚህ ከሃይማኖት አባቶች፣ ከመንግሥት፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከማኅበራት፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ከወጣቱ ትውልድ፣ ከፖለቲከኞች፣ ወዘተ ጀምሮ ሁሉም ድርሻቸውን በአግባቡ ሊወጡ ይገባል፡፡

# ስለዚያችም ምድር ክፉ የተናገሩ ሞቱ

*(ዘኍ.፲፬፥፴፯)*

## ዐውደ ስብከት

*ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን*

እግዚአብሔር አምላካችን የሰውን ልጅ ከፍጥረታት ሁሉ አልቆና አክብሮ በአርአያው ሲፈጥረው ስሙን ቀድሶ ክብሩን እንዲወርስ ነው። ስሙን ቀድሶ ክብሩን ይወርስ ዘንድ የሚያስችሉ ሕዋሳትንም በሚገባ አድሎታል። የተሰጠውን ሕዋሳት በአግባቡ ቢጠቀምባቸው ክብርን ያገኛል። ዐይኑን በአግባቡ ቢጠቀምበት መጻሕፍትን አንብቦ፣ መልካም ነገርን ሠርቶ ይድንበታል፣ ይጸድቅበታል። በአግባቡ ካልተጠቀመበት ግን ሞትን ያስከትላል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ትምህርት በቅዱስ ወንጌል "ቀኝ ዐይንህ ብታስትህ ከአንተ አውጥተህ ጣላት፤ ሁለት ዐይና ሆነህ ወደ ገሃነመ እሳት ከምትገባ ይልቅ አንድ ዐይና ሆነህ ወደ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና" (ማቴ.፭፥፳፱) ተብሎ የተመዘገበው እግዚአብሔር በሰጠን የአካል ክፍል ልንጠቀምበትም ልንጎዳበትም እንደምንችል ሲያስተምረን ነው። የዐይንን እንደማሳያ እንደተመለከትን ሁሉ የአንደበትም የሌላውም የሰውነት ክፍሎቻችን እንዲሁ ነው። በአንደበታቸው የተጠቀሙትንና የተጎዱትን በዚህ ጽሑፍ እንመለከታለን። ለዚህ መነሻ እንዲሆነን አንድ ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ እናንሣ።

"ምድሪቱንም ሊሰልሉ ሙሴ ልኮአቸው የተመለሱት ሰዎች ስለርስዋ በማኅበሩ ሁሉ ፊት አጕረመረሙ። ስለዚያችም ምድር ክፉን ነገር ተናገሩ፤ ስለዚያችም ምድር ክፉ የተናገሩ እነዚያ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት በመቅሠፍት ሞቱ፤ ምድሪቱ ግን መልካም ነበረች። ነገር ግን ምድሪቱን ሊሰልሉ ከሄዱ ሰዎች የነዌ ልጅ ኢያሱና የዮፎኒ ልጅ ካሌብ በሕይወት ኖሩ።" (ዘኍ.፲፬፥፴፮-፴፯) እንዲል። በዚህ ምንባብ ላኪ፣ ተላኪ. መልእክት፣ የመልእክት ምክንያት፣ ተላኪዎች ሲመለሱ ይዘውት የተመለሱት ጉዳይ ወዘተ ይዳሠሣሉ።

**፩. ላኪ፦** በዚህ ምንባብ የመልእክቱ ባለቤትና መልእክተኞችን የላከው እስራኤልን ከግብፅ ምድር አውጥቶ ወደ ከነዓን እየመራ ሊወስዳቸው ለዚህ አገልግሎት የተጠራው ሙሴ ነው። ሙሴ በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ እስራኤልን ከፈርዖን ግዞት፣ ከግብፅ ባርነት ያድን ዘንድ በመልካም ጥበቃው ከሞት ያዳነው ሰው ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን ይታደጋቸው ዘንድ ሙሴን ለምክንያትነት አዘጋጅቶታልና በሰው ዘንድ እጅግ የሚከብድ ፈተና ቢደርስበትም ሁሉን እንድንችል የሚያደርግ እግዚአብሔር እየረዳው ፈተናውን ሁሉ አልፎ እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ለማውጣት፣ ባሕረ ኤርትራን ለማሻገር፣ በበረሃ እየመገበ ለመምራት በቅቷል። እንደመሪነቱም ከነዓን ከመግባታቸው በፊት ስለከነዓን መረጃ ያስፈልጋቸው ስለነበር ዐሥራ ሁለት ሰላዮችን ላከ።

ሙሴ በዚያ ዘመን ማለትም ትምህርት አልተስፋፋም፣ ቴክኖሎጂ አልነበረም፣ ሥልጣኔ አልዳበረም፣ ወዘተ በሚባልበት ዘመን ሰላዮችን አዘጋጅቶ ልኳል። ይህን ተግባር በአሁኑ እይታ ብንመለከተው ሙሴ በዚያ ጊዜ የመረጃና ደኅንነት መሥሪያ ቤት አቋቁሞ ነበር ማለት ነው። በሰዎቹ አስተሳሰብ ወንድ ልጅ እንዳናይ በተባለበት ዘመን ከመታየት አልፎ እንዲህ ያለ ለምክንያት ድኅነት የሚበቃ እጅግ ጥበበኛና ታላቅ ሰው ተገኝቷል።

**፪. ተላኪ፦** የሙሴን መልእክት ይዘው ወደ ከነዓን ያቀኑት አካላት ዐሥራ ሁለቱ ሰላዮች ናቸው። እነዚህ አካላት የተላኩት እነርሱን ሊመራቸው እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ በሾመው በሙሴ ነው። የተላኩበት ቦታም በአግባቡ ደርሰዋል። በእግዚአብሔር ቸርነት በረአብ የደግነት ሥራ ምክንያት ከጠላት ድነው ወደ ሀገራቸው ገብተዋል። የሄዱበትንም ጉዳይ ፈጽመው ያዩትንና የተመለከቱትን እንደተረዱበት መጠን ይዘው ተመልሰዋል።

**፫.የተላኩበት ቦታ፦** እስራኤል ይወርሷት ዘንድ አስቀድሞ እግዚአብሔር አምላክ ለአባታችን ለአብርሃም "ይህችን

ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ” (ዘፍ.፲፪፥፯) በማለት እንደተናገረው ይወርሷት ዘንድ ተስፋ ወደሚያደርጓት ወደ ከነዓን ነው፡፡ ከነዓን ደግሞ የተስፋይቱ ምድር እየተባለች የምትጠራዋ፣ እስራኤላውያን እንወርሳታለን ብለው በተስፋ የአርባ ዓመት የእግር ጉዞ የተጓዙባት ናት፡፡ እስራኤላውያን ከነበረባቸው የፈርዖን ግዛት ለመውጣትና በነፃነት ለመኖር፣ የሚፈልጓትን ከነዓንን ለማግኘት የቀኑ ሐሩር የሌሊቱ ቊር ተፈራረቀባቸው፡፡

ይህች የከነዓን ምድር እንወርሳታለን ብለን በተስፋ የምንጠባበቃት የገነት ምሳሌ ናት፡፡ ሊቃውንቱ በትርጓሜ እንዳስረዱን ግብፅ የሲኦል ምሳሌ ስትሆን ከነዓን ደግሞ የገነት ምሳሌ ናት፡፡ ቤተ ክርስቲያንም በምድር ያለች ገነት ትባላለች፡፡ ስለዚህ ስለከነዓን ክፉ ያወሩት እንደ ሞቱ ዛሬም በምድር ያለች ገነት ስለተባለችዋ ስለ ቤተ ክርስቲያን ክፉ ወሬን የሚያመላልሱ መጨረሻቸው ሞት ይሆናል፡፡

ወደ ተስፋይቱ ምድር ተልከው መከራውን አጉልተው በማሳየት የሚያስፈራና የሚያጠራጥር ክፉ ወሬ ያመጡ እንዳሉ ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ያሉ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቸርነት ያልተረዱ ወዮ ላችሁ” የሚሉ በቅዱስ ወንጌል “እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ፡፡ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ የዋህ ነኝና፤ ልቤም ትሑት ነውና፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍትን ታገኛላችሁ፡፡ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና፡፡” (ማቴ.፲፩፥፳፰-፴) በማለት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረውን ትምህርት በመዘንጋት ሰውን ወደ ንስሓ የሚመልስ ትምህርት ከማስተማር ይልቅ ፈርቶና ተስፋ ቆርጦ እንዲሸሽ የሚያደርጉ ብዙ ናቸው፡፡

**፩. የተላኩበት ምክንያት፡-** ሰዎቹ ወደ ከነዓን የተላኩት ሊሰልሉ ነበር፡፡ ሙሴ ዐሥራ ሁለቱንም ሰላዮች ሲልክ ምድሪቱ ውስጥ ወይም ከነዓን ውስጥ ያለውን ሁኔታ ቀድሞ መረዳት ስለፈለገ ነበር፡፡ ከላይም እንደተገለጸው ሙሴ ያደረገውን ሥራ ማለትም እንደ ዛሬው ሥልጣኔው ባልተስፋፋበት ዘመን አስቀድሞ መረጃን መሰብሰብ እንደሚያስፈልግ፣ ምን አልባትም በየዋህነት ቢሄዱ ሊያጋጥማቸው የሚችል ችግር እንዳለ መረዳት በዚህ ዘመን ሁኔታ ሲመዘን እጅግ የሚደንቅ ነገር ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ዛሬም ቢሆን በእያንዳንዳችን ሕይወትም ሆነ እንደቤተ ክርስቲያን ነገ ምን መልካም ነገር ወይም ክፉ ነገር ሊገጥም ይችላል ብሎ ማሰብ አስፈላጊ እንደሆነ የሚያስተምረን ነው፡፡

ይህ ሲባል ግን በቅዱስ ወንጌል የተጻፈውንም መዘንጋት የለብንም፡፡ በቅዱስ ወንጌል “እናንተስ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል፡፡ ለነገ አትጨነቁ፤ ነገ ለራስዋ ታስባለችና፤ ለቀኒቱ ክፋቷ ይበቃታል” (ማቴ.፮፥፴፫-፴፬) ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ይህ ማለት ግን አታስቡ ማለት አይደለም፡፡ ፈልጉ የሚሉና አትጨነቁ የሚሉ ቃላት መኖራቸውን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ ፈልጉ ከተባልን እናስባለን፡፡ ደግሞም የሚያስብ ልቡና ሰጥቶ አታስቡ የሚል አምላክ አይደለም፡፡ ከአቅም በላይ መጨነቅ ግን አያስፈልግም፣ አይገባምም፡፡ መጨነቅና ማሰብ እጅግ የተለያዩ መሆናቸውንም መረዳት ያስፈልጋል፡፡

> **“እናንተስ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል፡፡ ለነገ አትጨነቁ፤ ነገ ለራስዋ ታስባለችና፤ ለቀኒቱ ክፋቷ ይበቃታል”**

**፫. መልክተኞች ያመጡት ነገር፡-** መልክተኞቹ ሀገሪቱ ላይ ስላለው የኃይል አሰላለፍ፣ የጦር ሁኔታ፣ የሀገሪቱን ለመኖር ምቹ መሆን በአግባቡ ተመልክተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ያለውን ሁኔታ የተረዱበትና የተገነዘቡበት መጠን የተለያየ ነበር፡፡ በዚህም የተነሣ ይዘውት የመጡት ወሬ የተለያየ ነው፡፡ ከሬሎቹ (ዐሥሩ) ክፉና አስደንጋጭ ወሬ ሁለቱ ግን ተስፋ የሚሰጥ መልካም ወሬ አመጡ፡፡

**ሀ. ክፉ ወሬ ያመጡ መልክተኞች፡-** ስለሀገሪቱ ሰዎች ኃያልነትና አስፈሪነት የሚገልጽ ክፉ ወሬን ያመጡት ዐሥሩ መልክተኞች ናቸው፡፡ ክፉ ወሬ ለማንም የማይበጅ ሀገርን የሚያጠፋ ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ ክፉና ሐሰተኛ ወሬን መስማት እንደሌለበት ለሊቀ ነቢያት ሙሴ ተነግሮት ነበር፡፡ "የሐሰተኛ ወሬን አትቀበል፤ ከዐመፀኛ ጋር አትቀመጥ፡፡ ለዐመፅ ከብዙ ሰው ጋር አንድ አትሁን፤ ፍርድንም ለማጣመም ከብዙ ሰው ጋር አትጨመር" (ዘፀ.፳፫፥፩-፪) እንዲል፡፡

ስለ ከነዓን ክፉ ወሬ ያመጡት ሰዎች የእግዚአብሔርን ቸርነት በአግባቡ ያልተረዱት ናቸው፡፡ የእግዚአብሔርን ቸርነት በአግባቡ ቢረዱት ኑሮ ባሕር ከፍሎ ጠላት ገድሎ፣ መና አውርዶ ደመና ጋርዶ፣ ዐለት ሰንጥቆ ውኃ አፍልቆ እየመገበና እየጠበቀ ከግብፅ ምድር አውጥቶ በበረሃ እየመራቸው ያለውን አምላክ ባልተጠራጠሩትና የሰዎችን ኀያልነት አጉልተው ባልተናገሩ ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን ቸርነት በአግባቡ የተረዱት ኢያሱና ካሌብ ግን ምንም እንኳን ሰዎቹ ኀያላን ቢሆኑም በእግዚአብሔር ቸርነት እንወርሳታለን በማለት ተናገሩ፡፡

**ለ. መልካም ወሬ ያመጡት፡-** የተስፋይቱን ምድር ሊወርሱ እንደሚችሉ በተስፋ የተናገሩ ኢያሱና ካሌብ ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር ሰው ሁል ጊዜ የሚናገረው ለሰው መልካም የሆነውን ነው፡፡ ሰው የሚድንበትን፣ ሰው የነገ ተስፋ የሚሰንቅበትን፣ ወደ ፊት ብሩህ ተስፋ የሚይዝበትን መልካም ወሬ ያወራል፡፡

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ "ሰላምን የሚያወራ መልካም የምሥራችንም የሚናገር፣ መድኃኒትንም የሚያወራ፣ ጽዮንንም አምላክሽ ነግሦአል፤ የሚል ሰው እግሩ በተራሮች ላይ እጅግ ያማረ ነው፡፡" (ኢሳ.፶፪፥፯) በማለት ተናግሯል፡፡ መልካም ነገርን የሚናገር ሰው አንደበቱ ብቻ ሳይሆን እግሩም ያማረ ነው ይባልለታል፡፡ አንድ ሰው ይመጣል ተብሎ ባልታሰበበት ጊዜ ሲመጣ "በእውነት አመጣጥህ መልካም ነውን" ተብሎ ይጠየቃል፡፡ ምን አልባትም በመጣበት ወቅት መልካም ነገር የማይከሠት ከሆነ ሰውየው ሳይቀር "እግረ ደረቅ"፣ "ገደ ቢስ" ይባላል፡፡ ከዚህ አልፎ ደግሞ የሚናገረው ነገር ሰው የሚያስቀይም ከሆነ እጅግ የተጠላ ይሆናል፡፡

ኢያሱና ካሌብ ግን የተመለከቱት ነገር ምንም የሚያስፈራ ቢሆንም በእግዚአብሔር ቸርነት ሁሉ እንደሚቻል አምነው እንወርሳታለን በማለት መልካም ነገርን ተናገሩ፡፡ እንደነዚህ መልካም ነገርን መናገር የሚችሉትን ሰዎች ልበ አምላክ ዳዊት "የጻድቅ አፉ ጥበብን ይማራል፤ አንደበቱም ጽድቅን ይናገራል፡፡ የአምላኩ ሕግ በልቡ ውስጥ ነው፡፡" (መዝ.፴፮፥፴) በማለት ይገልጻቸዋል፡፡ መልካም ወሬ የሚባለውም ይህ ነው፡፡

**ሐ. የክፉ ወሬ ውጤት፡-** ስለ ተስፋይቱ ምድር ስለ ከነዓን ክፉ ወሬ ያመጡት መጨረሻቸው ሞት ነበር፡፡ የክፉ ነገር ውጤቱ መቼም ቢሆን ሞት ነው፡፡ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮሜ ምእመናን በላከው መልእክቱ "ለኃጢአት ትገዙ በነበረበት ጊዜ ከጽድቅ ነፃ ነበራችሁና፡፡ በዚያን ጊዜ ሥራችሁም እነሆ ዛሬ ታፍሩበታላችሁ መጨረሻው ሞት ነውና" (ሮሜ ፮፥፳፫) በማለት እንደተናገረው ክፉ የተናገሩት አካላት ውጤታቸው ሞት ሆኗል፡፡ ነገሩ ሐሰትና ክፉ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን የሚነገርበት መንገድና ዐውድም በራሱ ወሳኝነት አለው፡፡

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልጇን ከሄሮድስ ለማዳን ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር በተሰደደች ጊዜ መንገድ ላይ ደክሟቸው እንደተቀመጡ የዮሴፍ ልጅ ዮሳ ደረሰባቸው፡፡ ዮሳም ወዲያውኑ እንደደረሰ "የቤተ ልሔም ሕፃናት አልቀዋል፤ እናንተ እዚህ ተቀምጣችኋል" በማለት ፈጥነው ተነሥተው ጉዟቸውን እንዲቀጥሉ ሲናገር ምንም እንኳ እርሱ የተናገረው ለእነርሱ ከማዘን አንጻር ቢሆንም ጌታችን መድኃኒታችን ግን እናቴን አስደንግጠሃታልና ዳግም

እስክመጣ ድረስ ከዚች ደንጊያ ላይ ዕረፍ ብሎ እንዲሞት አድርጎታል፡፡ ይህንንም በማኅሌተ ጽጌ እመቤታችን ድንግል ማርያምን ያመሰገነው አባ ጽጌ ድንግል "ዮሳ ወልደ ዮሴፍ ምንተ ገብረ ኃጢአተ፣ ዘያደነግጽኪ ዜና በእንተ ዘአምጽአ ግብተ፣ አኮኑ ጻድቅ በትእዛዘ ጽጌኪ ሞተ፤ የዮሴፍ ልጅ ዮሳ ምን ኃጢአት ሠራ? የሚያስደነግጥሽ ዜናን ድንገት ስላመጣ ጻድቁ በልጅሽ ትእዛዝ ሞቷልና፡፡" (ማሕሌተ ጽጌ) በማለት ገልጾታል፡፡

> **"ምላስ እሳት ናት፤ እነሆ ትንሽ ምላስ በሰውነታችን ውስጥ ዐመፅ የተመላበት ዓለም ናት፤ ሥጋችንን ትበላዋለች፤ ውሳጣዊ ሰውነታችንንም ትጠብሰዋለች፤ ከገሃነም ይልቅ ታቃጥላለች፡፡ የአራዊትና የወፎች የተንቀሳቃሾችና በባሕር ያለ የፍጥረት ወገን ሁሉ ለሰው ይገዛል፤ ተገዝቷልም፡፡ የሰውን ምላስ ግን መግዛት የሚቻለው የለም፤ ክፉ ናት ዐቅምም የላትም፤ የሚገድል መርዝንም የተመላች ናት፡፡ በእርስዋ እግዚአብሔር አብን እናመሰግነዋለን፤ በእርስዋም በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ ሰውን እንረግመዋለን"**

ዮሳ የተናገረው ነገር እውነት ነው፡፡ ግን የተናገረበት ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን ነበር፡፡ ዛሬም ጉዳዩ እውነታ ሊኖረው ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ የምንናገርበት መንገድ፣ እውነትም ቢሆን ጊዜው ቦታውና ሁኔታው ተገቢ ካልሆነ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝንና የምንድንበት ሳይሆን የምንሞትበት ይሆናል፡፡ ዐሥሩ ሰላዮች የተናገሩት እውነት ነበር ሰዎቹ የሚያስፈሩ፣ የሚያስጨንቁ ነበሩ፤ ግን የተናገሩበት መንገድ የእግዚአብሔርን ቸርነት የዘነጉበት ሁኔታ ስለሆነ ያመጡት መረጃ የሞታቸው ምክንያት ሆናቸው፡፡

**መ. የመልካም ወሬ ውጤት፡-** መልካም ወሬን ያመጡት ሁለቱ ሰላዮች ማለትም ኢያሱና ካሌብ ውጤታቸው በሕይወት መኖር ነበር፡፡ እውነትንና መልካም ነገርን የያዘ ለጊዜው ደካማ ቢመስልም ፍጻሜው ግን ያማረ ይሆናል፡፡ ይህን በተመለከተ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "በክብርና በውርደት፣ በምርቃትና በርግማን እንደ አሳቾች ስንታይ እውነተኞች ነን፡፡ እንደማይታወቁ ስንታይ የታወቅን ነን፤ እንደ ሰነፎች ስንታይም ልባሞች ነን፤ እንደሙታን ስንታይ ሕያዋን ነን፤ የተቀጣን ስንሆንም አንገደልም፡፡ ኀዘንተኞች ስንሆን ዘወትር ደስተኞች ነን፤ እንደ ድሆች ስንሆን ብዙዎችን እናበለጽጋለን፤ ምንም የሌለን ስንሆን ሁሉ በእጃችን ነው" (፪ቆሮ.፮፥፰-፲) በማለት እንደገለጸው ምንም በሰው ዘንድ ጠቀሜታው ፈጥኖ ባይታይም መጨረሻው ግን ያማረ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ "እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን ስለእርሱ መልስ ይሰጡበታል፡፡ ከአነጋገርህ የተነሣ ትጸድቃለህ፤ ከአነጋገርህም የተነሣ ይፈረድብሃልና" በማለት እንዳስተማረው የምንናገረው ነገር በሕይወት ለመኖርና ላለመኖር እጅግ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ መልካም መናገር ያስከብራል፣ ያሸልማል፤ በሕይወት እንድንኖር ያደርገናል፡፡ በአንጻሩ ክፉ መናገር ደግሞ ያዋርዳል፣ ያስቀጣል፣ ሞትንም ያስከትላል፡፡

ዛሬም የሆነውን የሚደብቁ ያልሆነውን ሆነ የሚሉ፣ ሰውን ወደ መልካም ነገር ሳይሆን ወደ ግጭትና ወደ ጦርነት እንዲገፋፉ የሚያደርጉ ብዙ ሰዎቹ ናቸው፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ የዕለተ ምጽአትን ምልክት ለጠየቁት ደቀ መዛሙርቱ "ጦርነትን የጦርነትንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠንቀቁ፤ አትደንግጡ፤ ነገር ግን ፍጻሜው ገና ነው"

(ማቴ.፳፬፥፯) ፤ "ጦርነትንና የጦርነትንም ወሬ በሰማችሁ ጊዜ አትደንግጡ፤ ይህ ይሆን ዘንድ አለውና፤ ነገር ግን ፍጻሜው ገና ነው።" (ማር.፲፫፥፯) በማለት አስረድቷቸዋል። ስለዚህ በየቦታው የጦርነት ወሬ የሚያወሩ፣ የሆነውን ሳይሆን ያልሆነውን እየተናገሩና እየጻፉ ሰውን ከሰው የሚያጋጩ በርካቶች ናቸው።

ሐዋርያው ያዕቆብ "ምላስ እሳት ናት፤ እነሆ ትንሽ ምላስ በሰውነታችን ውስጥ ዐመፅ የተመላበት ዓለም ናት፤ ሥጋችንን ትበላዋለች፤ ውሳጣዊ ሰውነታችንንም ትጠብሰዋለች፤ ከገሃነም ይልቅ ታቃጥላለች። የአራዊትና የወፎች የተንቀሳቃሾችና በባሕር ያለ የፍጥረት ወገን ሁሉ ለሰው ይገዛል፤ ተገዝቷልም። የሰውን ምላስ ግን መግዛት የሚቻለው የለም፤ ክፉ ናት ዕቅምም የላትም፤ የሚገድል መርዝንም የተመላች ናት። በእርስዋ እግዚአብሔር አብን እናመሰግነዋለን፤ በእርስዋም በአርአያ እግዘአብሔር የተፈጠረ ሰውን እንረግመዋለን" (ያዕ.፫፥፮-፱) በማለት አንደበታችን ምን መሆን እንዳለበት ያስረዳናል። ስለዚህ አንደበታችን የተፈጠረልን ልንናገርበት ነው። ይሁን እንጂ የምንናገረው ግን የእግዚአብሔርን ቃል እና መልካም የሆነውን ሁሉ ሊሆን ይገባል።

ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድም በድጓው "ይጹም ዐይን ይጹም ልሳን እዝንኒ ይጹም እምሰሚዐ ኅሱም በተፋቅሮ፤ ዐይን ይጹም፣ አፍም ይጹም ጆሮም ክፉ ከመስማት ይጹም" በማለት የተናገረው ኅዋሳችን የተሰጠን መልካም ነገርን ልንጠቀምበት ነው። ነገር ግን ከመጠቀም አልፎ ልንጎዳበት የምንችለውን ሥራ ከመሥራት ግን መቆጠብ ይኖርብናል። መጾም የሚባለውም ከእህልና ከውኃ መከልከል ብቻ እንዳልሆነ ሊቁ ነግሮናል። ጎረቤቶቻችንን የሚያሳዝን ወሬን ከመናገር፣ ዐይናችን የእኛ ያልሆነውን ከመመልከትና ባልንጀራችንን ከማሳዘን ወዘተ. ሁሉን መከልከል ይኖርብናል።

የሚሆነውንም የማይሆነውንም ነገር እየተናገሩ ሰውን ከመጉዳት ይልቅ ያለንበት ወቅቱ አስቸጋሪ ነውና ይህን አስቸጋሪ ወቅት ማለፍ እንድንችል መጾም ያስፈልጋል። እንዲሁ የሰዎችን አእምሮ የሚጎዳ ክፉ ወሬን ከምነግራቸው በችግራቸው ደርሰን ልናጽናናቸው፣ ካለባቸው ረኀብና ጥም ልንታደጋቸው ይገባል። በመጽሐፈ ጦቢት "ከገንዘብህ ምጽዋት ስጥ፤ ምጽዋትንም በምትመጸውት ጊዜ በገንዘብህ አትንፈግ፤ ከድኃም ፊትህን አትመልስ። እግዚአብሔርም ፊቱን ከአንተ አይመልስም። ባለህ መጠን የሚቻልህን ያህል ምጽዋት አድርግ። ጥቂትም ቢሆን ለመስጠት አትፈር፤ ምጽዋት መስጠት መልካም ድልብን ታደልብልሃለችና። ምጽዋት በመከራ ቀን ከሞት ታድናለችና። ወደ ጨለማም ከመሄድ ትጠብቅሃለችና። ምጽዋትም ለሚያደርጋት ሁሉ በልዑል ፊት መልካም ስጦታ ናት።" (ጦቢ. ፫፥፯-፲፩) ተብሎ እንደ ተነገረ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ለእኛም የሚጠቅመንን መልካም ሥራ መሥራት ይኖርብናል።

እንዲሁም ሊቁ ቅዱስ ያሬድ "ብፁዕ ውእቱ ዘኮነ ኬንያ ለነፍሱ፤ ብፁዕ ውእቱ ዘተግኅሠ እምኃጢአት፤ ብፁዕ ውእቱ በአፉሁ ዘኢተናገረ ከንቶ፤ ብፁዕ ውእቱ በከመ በዓቱ ዘኮኖ ፀዓቱ፤ ብፁዕ ውእቱ ዘኮና ልቡ ሠረገላ ለጸሎት፤ ብፁዕ ውእቱ፤ ለነፍሱ ጥበበኛ የሆነ ብፁዕ ነው፤ ከኃጢአት የራቀ ብፁዕ ነው፤ በአፉ ከንቱ ነገርን ያልተናገረ ብፁዕ ነው፤ መጨረሻው እንደ መጀመሪያው የሆነለት ብፁዕ ነው፤ ልቡ የጸሎት ሠረገላ የሆነለት ብፁዕ ነው።" (ጾመ ድጓ ዘገብር ኄር) በማለት ከኃጢአት የራቀ፣ በአፉ ከንቱ ነገርን ያልተናገረ፣ ልቡ የጸሎት ሠረገላ የሆነለት፣ ንዑድ ክቡር የተመሰገነ መሆኑን ያስረዳናል።

በአጠቃላይ ሰው በዚህ ዓለም ጊዜያዊም ቢሆን ይኖርበት ዘንድ በተሰጠው በዚህች ምድር ሲኖር የሚገባውን እየሠራ የሚገባውን እያገኘ፣ ለማያልፈውና ዘለዓለማዊው ዓለም መሥራት እንዳለበት መረዳት የግድ ነው። ሰው በማኅበር ይኖር ዘንድ የተፈቀደለት ብቻ ሳይሆን የሚያስፈልገውም ነገር ነው። ማንም በራሱ ምሉእ አይደለም። ስለዚህ ከራሱ የሚጎድለውን ከሌላው ያገኛል። እርሱ የጎደለውን ከሌላ እንደሚያገኝ ሁሉ በአንጻሩ እርሱም ለሌላ የሚሰጠው ብዙ ነገር አለው። በዚህ ጊዜ ግን የሚገባውን እየተናገረ፣ ከክፉ ነገር ርቆ፣ ሰውነቱን ከኃጢአት አርቆ፣ በአንደበቱ፣ በዐይኑ፣ በእጁ፣ በእግሩ ወዘተ በሰውነት ክፍሎቹ ሁሉ ከሚመጣ በደል ታግሦ መኖር አለበት። በሃይማኖት ጸንቶ በጎ ምግባር ሠርቶ ከሰው ጋር በፍቅር ኑሮ፣ በሰውም በእግዚአብሔርም ዘንድ ተወዳጅ ሆኖ መኖር ያስፈልጋል። እንዲህ ያደረገ ሰው መጨረሻው ዘለዓለማዊ ሕይወት ያለበትን ሰማያዊውን ርስት መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳል። ሁላችንንም ስሙን ቀድሰን፣ መንግሥቱን ወርሰን ለመኖር ያብቃን አሜን።

# “እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ”

(ዮሐ.፲፪፥፴፪)



በዲ/ን ተስፋዬ ምትኩ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚች ምድር የመጣው፣ ዞሮ ያስተማረውና በመስቀል ተሰቅሎ የሞተው ሁሉን ወደ ራሱ ይስብ ዘንድ ነው፡፡ በመሆኑም ወደዚህ የመጣበትንና ዓለምን ያድን ዘንድ የወደደበትን ልዩ ጥበብ “እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ” በማለት ነገረን፡፡ ይህን የጌታችንን ንግግር ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ ሲያብራራው “በምን ዓይነት ሞት ይሞት ዘንድ እንዳለው ሲያመለክታቸው ይህን ተናገረ” (ዮሐ.፲፪፥፴፫) ብሏል፡፡

ስለዚህ ከፍ ከፍ ያልሁ እንደሆነ ማለቱ ከምድር ከፍ ከሰማይ ዝቅ ብሎ መሰቀሉን ለመናገር ነው፡፡ ወደ እኔ እስባለሁ ማለቱ ደግሞ ሰውን በግብርም በክብርም እኔን እንዲመስል አደርጋለሁ ማለቱ ነው፡፡ በግብር መምሰል ስንል የሰው ልጅ አዳምና ሔዋን የዲያብሎስ አገልጋዮች ነን ብለው በፈረሙት የዕዳ ደብዳቤ መሠረት ለ፶፻፭፻ ዘመን የዲያብሎስ ተገዥዎች ሆነው ነበር፡፡ ይህ የዕዳ ደብዳቤ ደግሞ በክርስቶስ መስቀል የሚደመሰስ መሆኑን ሲያመለክት በግብር እንዲመስሉኝ አደርጋለሁ አለ፡፡ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለቆላስይስ ምእመናን በላከው መልእክቱ “በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፡፡ እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል” በማለት እንዳስረዳን፡፡ (ቆላ.፪፥፲፬)

በክብር ወደ እኔ አቀርባለሁ ማለቱ ደግሞ በተዋሐደው የአዳም ሥጋ ተሰቅሎ፣ ሞቶ፣ ሞትንም ድል አድርጎ በመነሣት በዚያው ሥጋ ወደ ሰማይ ዐርጎ በአባቱ ቀኝ ይቀመጣልና፡፡ የሰው ሥጋ በአብ ቀኝ የመቀመጥን ክብር የሚያገኝ መሆኑን ሲያጠይቅ ይህን ተናግሯል፡፡ “እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሠራር፥ ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል” እንዲል፡፡ (ፊል.፫፥፳፩) በሌላ በኩል  የአዳምን ዕዳና በደል በመስቀል ላይ በከፈለው የደም ካሳ ከደመሰሰ በኋላ በቀኙ ለተሰቀለው ሽፍታ “ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ” እንዳለው፡- የሰው ልጅ ሁሉ ከዲያብሎስ ተገዥነትና ከሲኦል ባርነት ነፃ ወጥቶ በክብር ከፍ ከፍ እንዲል አደርጋለሁ ሲለን ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ አለ፡፡ (ሉቃ.፳፫፥፵፫) እንዲሁም ጌታ በመስቀል ካሳ እስከከፈለበት ጊዜ ድረስ የዲያብሎስ ባሪያዎች ተብለን እንጠራ የነበርን የሰው ልጆች ሁሉ ከካሳ በኋላ በክርስቶስ ስም ክርስቲያን በወልድ ስም ውሉደ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ስም መንፈሳውያን ተብለን እንድንጠራ አድርጎናልና ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ አለ፡፡

**ለመሆኑ ክርስቶስ ሁሉን ወደ ራሱ የሳበበት ምሥጢር ምንድን ነው**

### ዕርቅን በማድረግ፡-

ጥል ባለባቸው ሁለት ሰዎች መካከል ሰላም ሲሆን ዕርቅ ሆነ ይባላል፡፡ የሰው ልጅም በአዳም ኃጢአት ምክንያት ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶ ለ፶፻፭፻ ዘመናት መኖሩ ይታወቃል፡፡ ሰው ከእግዚአብሔር በመጣላቱም ምክንያት፣ ሰውና መላእክት፣ ሕዝብና አሕዛብ፣ ነፍስና ሥጋ ተጣልተው ለዘመናት ኖረዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ የታረቁት በወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን ነው፡፡

እንደሚታወቀው የሰው ልጅ በነፍስም በሥጋም ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን የሰውን ነፍስና ሥጋ ከመለኮቱ ጋር አዋሐዶ ፍጹም ሰው ሆነ፤ ሥጋንም ፍጹም አምላክ አደረገው፡፡ በዚህም ዕርቀ ሰላም ሆነ፡፡ መቼም አንድ አካል ከራሱ ጋር ተጣላ እንዳይባል ሁሉ መለኮትም ከነፍስና ሥጋ ጋር ተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ሆኗልና ፍጹም ዕርቅ ሆኗል፡፡ አካል ከአካል ከተዋሐደ ባሕርይ ከባሕርይ አንድ ከሆነ ጠብ ክርክር ጥላቻና አለመስማማት አይኖርምና፡፡ ኦርቶዶክሳዊት

ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስን የማስታረቅ ሥራ የምታስተምረው በዚህ መንገድ ነው እንጂ "ክርስቶስ እርሱ ሦስተኛ ሆኖ ሌሎች ሁለት ወገኖችን አስታረቀ" ብላ አታስተምርም። ክርስቶስን ሰው ያሰኘውን የአዳምን ሥጋ፣ ሞትና መቃብር፣ መከራና ሥቃይ የተፈረደበትን የአዳምን ሥጋ "አዳም ሆይ ስለ ጥፋትህ ሞት ይገባሃል" ብሎ ከፈረደው መለኮትነቱ /እግዚአብሔርነቱ/ ጋር ማስታረቁን /መዋሐዱን/ ታስተምራለች እንጂ። ክርስቶስ የሚለውም ስም አምላክም ሰውም መሆኑን ይገልጽልናልና። ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው በሁለተኛው መልእክቱ ላይ ይህን ሲያብራራው "እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር" ብሎ ጽፎልናል። (፪ኛ ቆሮ.፭፥፲፰-፳)

ክርስቶስ የሚለው እግዚአብሔር ወልድ ሥጋ አዳምን ከተዋሐደ በኋላ የተሰጠው ስም ነው። በሌላ አባባል እግዚአብሔር የሚለው ስም ውስጥ ክርስቶስም አለበት። እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ አስታረቀ ማለትም እግዚአብሔር በክርስቶስነቱ ከዓለም ጋር ታረቀ ማለት ነው። አንድም እግዚአብሔር ክርስቶስ ተብሎ ራሱ ከዓለም ጋር ታረቀ ማለት ነው።

**ክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር ያስታረቀው ራሱ መሥዋዕት አቅራቢ /ካህን/ ራሱም መሥዋዕት /የመሥዋዕት በግ/ ራሱም መሥዋዕት ተቀባይ ምሕረት አድራጊ /ይቅርታ አድራጊ/ ሆኖ ነው እንጂ እንደ አማላጅ ሥርዓት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሦስተኛ አካል ሆኖ መባና መሥዋዕት ይዞ በመቅረብ አይደለም።**

ክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር ያስታረቀው ራሱ መሥዋዕት አቅራቢ /ካህን/ ራሱም መሥዋዕት /የመሥዋዕት በግ/ ራሱም መሥዋዕት ተቀባይ ምሕረት አድራጊ /ይቅርታ አድራጊ/ ሆኖ ነው እንጂ እንደ አማላጅ ሥርዓት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሦስተኛ አካል ሆኖ መባና መሥዋዕት ይዞ በመቅረብ አይደለም። ይህም የተፈጸመው በዕለተ ዓርብ ከምድር ከፍ ከሰማይ ዝቅ ብሎ በተሰቀለ ጊዜ ነው። በዚህ አሕዛብን ወደ ራሱ ስቦ አቅርቧቸዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን እውነት ሲነግረን "እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፣ በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና። እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፣ በፊት የተለያችሁትን ክፉ ሥራችሁንም በማድረግ በሐሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ" ብሏል። (ቆላ.፩፥፲፱-፳፪)

## ፍቅሩን በመግለጥ

ፍቅሩን ገለጠ ስንል ሁለት ነገር ማለታችን ነው። አንደኛ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር መግለጥ ማለታችን ነው። ይህን ሲያስረዳ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "... ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና ይህም እግዚአብሔር ስለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" ብሏል። (ሮሜ ፭፥፰) ሁለተኛው ደግሞ የፍቅርን ምንነት በተግባር በማሳየት ነው።

ከክርስቶስ መገለጥ በፊት ሕዝቡ የሚያመልኳቸው ብዙ ጣዖታት ነበሩ። በርግጥ ዛሬም አሉ። እነዚህ ጣዖታት የማይናገሩ፣ ክፉም ሆነ ደግን ማድረግ የማይችሉ፣ የማያዩ፣ የማይሰሙ፣ የማይንቀሳቀሱ የሰው እጅ ሥራዎች ሲሆኑ የጣዖታቱ ሠሪዎችና አስመላኪዎች የሆኑት ካህናተ ጣዖትና ዐላውያን ነገሥታት ግን ጣዖታቱ እንደ ተናገሩና ውሳኔ እንዳስተላለፉባቸው አድርገው ተከታዮቻቸውን በብዙ ያስጨንቋቸው ነበር። ገንዘባቸውን ሁሉ እንዲያመጡ፣ ከብቶቻቸውን ሁሉ እንዲሠው፣ ልጆቻቸውን ጭምር ለጣዖታቸው መሥዋዕት አድርገው እንዲያቀርቡ ያደርጉ

ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክና ወዳጅ መሆኑን፣ በምእመናን ሞትና መከራ የሚደሰትና አማኞች ልጆቻቸውን፣ ከብቶቻቸውን እንዲሠውለት ከመጠየቅ ይልቅ አንድያ ልጁን አሳልፎ በመስጠት በእርሱ ሞትና ትንሣኤ ዓለምን የሚያድን አምላክ መሆኑን በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተረድተናል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ይህን እውነት ሲናገር "የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና፡፡" ካለ በኋላ "ፍቅር እንደዚህ ነው እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተስረያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም" በማለት ጽፎልናል፡፡ (፩ኛ ዮሐ.፬፥፺-፲፩)

> **"ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም"**

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ፍጹም ፍቅር ሲናገር "ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም" ብሏል፡፡ (ዮሐ.፲፭፥፲፫) በእውነቱ ለወዳጁ እንኳንስ ነፍሱን ገንዘቡን በደስታ የሚለግስ ማን ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ደግሞ ጠላቶቹ ነበርን እንጂ ወዳጆቹም አልነበርንም፡፡ "ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ታረቅን" እንዲል፡፡ (ሮሜ ፭፥፲) እንግዲህ ከዚህ ፍቅር በላይ ስቦ የሚያቀርበን ኃይል ምን ሊሆን ይችላል? ነፍሱን ከመስጠትስ በላይ የፍቅርን ጥልቀት የሚገልጽ ምን ይገኛል?

## የጥበበኞችን ጥበብ ከንቱ በማድረግ

ለሰው ልጅ ሲል ለዓለም ጥበበኞች ተገርፎ፣ ተገፎ፣ ምራቅ ተተፍቶበት፣ በጥፊ ተመትቶ፣ የአይሁድ ንጉሥ ሆይ ራስህን አድን እኛም አይተን እንመንብህ ተብሎ ተዘብቶበት፣ ተሰቅሎ የሞተውን አምላካችን ነው ብሎ መቀበል በዓለም ጥበበኞች ዘንድ ሞኝነት ነው፡፡ እኛን ክርስቲያኖችን ልዩ ከሚያደርጉንም ነገሮች አንዱ የምናመልከው ጌታ ስለ እኛ መሰቀሉንና መሞቱን ያለፍርሃት መመስከራችን ነው፡፡ ሌሎች ቤተ እምነቶች ግን ስለ አምላካቸው፣ ኃያልነት፣ ሁሉን ቻይነት፣... እንጂ ስለ ሞቱም ሆነ ስለመከራው ማውራት አይፈልጉም፡፡ እኛ የምናመልከው ጌታ ግን፣ በአምላካዊ ሥልጣኑና ኃይሉ የሚገዳደሩትን ጠላቶቹን ከመደምሰስ ይልቅ ተሸንፎ በፍቅር ማሸነፍን፣ ወዷል፡፡ ወዳጆቹ በፍቅር እንዲያከብሩትና እንዲያመሰግኑት መፍቀድ ብቻም ሳይሆን ጠላቶቹም በሰውነቱ የወደዱትን እንዲያደርጉበት የፈቀደ፣ ጠላቶችንም ከወዳጆቹ እኩል አድርጎ የወደደ ጌታ ነው ያለን፡፡ ይህን የመሰለ ጥበብ በዓለም ዘንድ የለም፡፡ ጥበበኞች ነን ለሚሉንም ይህን እውነታ ብንነግራቸው ሞኞች ይሉን ሆናል እንጂ አይረዱንም፡፡

የዓለም ጥበበኞች የሚያምኑት የሚገዳደሯቸውን ጠላቶቻቸውን፣ ከፊታቸው ዞር እንዲሉ በማድረግ ነው፡፡ በተለይም ስሕተታቸውን እየነገረባቸው የሚያስጨንቃቸውን ገዳይ እየቀጠሩ ከምድረ ገጽ ያጠፉታል፡፡ ቢነቃባቸው ደግሞ ጠበቃ ቀጥረው ይከራከራሉ፤ ዳኛን በጉቦ እየደለሉ፣ ለሐሰት ምስክሮች ገንዘብ እየከፈሉ ንጹሕነታቸውን ያውጃሉ፤ ከኅሊና ክስ ግን አምልጠው አያውቁም፡፡ ክርስቶስ ግን ሁሉን ቻይ አምላክ ሆኖ ሳለ አንዳችም ጥፋት ሳይኖርበት፣ ከአንደበቱ ቃል ሳይወጣ፣ እጆቹንም ዘርግቶ ሳይመታ ጠላቶቹን ማጥፋት እየቻለ ያለጥፋቱ ለሚከሱት "ንጹሕ ነኝ" ብሎ ስለራሱ መከራከርን እንኳን አልወደደም፡፡ የጠላቶቹን ፈቃድ ፈጽመላቸው እንጂ፤ በሰውነቱም የወደዱትን እንዲያደርጉ ፈቀደላቸው፡፡ ጠላቶቹ የወደዱትን በማድረጋቸው ረኩ፤ ወዳጆቹ ደግሞ በሞቱ የዘለዓለም ሕይወትን አገኙ፡፡ ጠላቶቹን ከመግደል ይልቅ እንደ ጠላቶቹ ፈቃድ በመሞት ለዓለም ሁሉ ሕይወትን ከመሆን በላይ ጥበብ የት ይገኝ ይሆን? በዚህም በማስፈራራትና በመግደል የሚገዙትን የዓለም ነገሥታትን ጥበብ ከንቱነትን አሳየ፤ ስለ በጎቹ ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ

እረኛ መሆኑንም በማስመስከሩ በጎቹን ሁሉ ወደ ራሱ ሳበ። "እኔ ከፍ ብዬ ብሰቀል ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ" ማለቱም ለዚህ ነው።

የክርስቶስ በቤተ ልሔም ዋሻ በከብቶች በረት መወለዱ፤ በዮርዳኖስ ወንዝ በፍጡሩ በዮሐንስ እጅ መጠመቁ፣ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ መጾሙ (መራቡ መጠማቱ)፣ በአህያ ውርንጭላ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ እና በመጨረሻም በዕፀ መስቀል ተሰቅሎ መሞቱ "በዚህች ዓለም ከእኛ በላይ ጥበበኞች የሉም" በሚሉት በግሪካውያን እና፣ "ለእግዚአብሔርና ለሕጉ ከእኛ በላይ ቅርብ የሆነ ሕዝብ በዚህ ምድር የለም" በሚሉት ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ዘንድ ትልቅ ሞኝነት ነው። በጸሐፍትና በፈሪሳውያን እምነት ክርስቶስ የሚመጣው በታላቅ ዙፋን ተቀምጦ፣ አክሊል ደፍቶ፣ ካባ ደርቦና በወታደር ታጅቦ ከሮማውያን ቅኝ ግዛትና ከጭቆና ነፃ ለማውጣት ነው። እርሱ ግን በሁለት ወንበዴዎች መካከል እርቃኑን ተሰቅሎ፣ ተገፎ፣ ተገርፎ፣ ተዋርዶ፣ ሞቶና ተቀብሮ የሚያድናቸው ሆኗል። ይህን ደግሞ እንደ ዓለም ጥበብ ስንመለከት ሞኝነት ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲያብራራ "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፣ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና። የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ የአስተዋዮችንም ማስተዋል እጥላለሁ ተብሎ ተጽፎአልና። ጥበበኛ የት አለ? ጻፊስ የት አለ? የዚች ዓለም መርማሪስ የት አለ? እግዚአብሔር የዚህችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበብዋ ስላላወቀች፣ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና። መቼም አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፣ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው" ብሏል። (፩ኛ ቆሮ.፩፥፲፰-፳፫)

ዛሬም መስቀሉን እንጨት፣ ጸበሉን ውኃ፣ እምነቱን አፈር፣ ታቦቱን እንጨት የሚሉ ሰዎች የዓለም ጥበበኞች ሞኞች ስለሆኑ ነው። እግዚአብሔር ግን የዓለምን ጥበብ ያፈርስ ዘንድ ዓለም በናቀው ነገር ላይ አድሮ ያድናል፤ ድንቅ ድንቅ ተአምራትንም ያደርጋል፤ ይመሰገንበታልም።

## የዲያብሎስን ጥበብ በመሻር

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ክርስቶስ ወደዚች ምድር የመጣበትን ትልቁን ዓላማ ሲያብራራ "የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ" ብሏል። (፩ኛ ዮሐ.፫፥፱) ይህ እንደምን ነው ቢሉ? ዲያብሎስ እንደ ጥበብ ተጠቅሞ አዳምንና ሔዋንን ያታለላቸው "ዕፀ በለስን" ከበላችሁ አምላክ ትሆናላችሁ" በማለት ነበር። ክርስቶስም ዲያብሎስ አዳምን የእንጨት ፍሬ በማብላት ድል በነሣው አንጻር በዕፀ መስቀል ተሰቅሎ ድል ነሥቶታል።

ዲያብሎስ አዳምንና ሔዋንን ዕፀ በለስን ከበላችሁ አምላክ ትሆናላችሁ ያለው ለሽንገላና ለማታለል ሲሆን ክርስቶስ ግን ዲያብሎስ አዳምን ለማሞኘት የተጠቀመበትን ሐሳብ በአምላካዊ ጥበቡ ወደ እውነት ቀይሮ በተዋሕዶ ሰው ሆኖ የሰውን ሥጋ አምላክ አደረገው። መለኮት በተዋሐደው ሥጋ ሞትንና መቃብርን ድል አድርጎ በመነሣት በሞትና በዲያብሎስ ላይ ሥልጣንን ሰጠን።

እንደ ዲያብሎስ ጥበብ በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው። የተረገመ ወይም ተግባሩ ርጉም የሆነ ሰው ደግሞ የተግባሩ ውጤት በሥጋው ወደ መቃብር በነፍሱም ወደ ሲኦል ወርዶ መከራ መቀበል ነው። ጌታችን ግን በዕፀ መስቀል ተሰቅሎ ሞትና መቃብርን ድል በማድረግ ነፍሳትን ከሲኦል ወደ ገነት መልሷቸዋል። ዲያብሎስ የሰውን ልጅ በማሞኘት ወደ ሞት ጎዳና ነበር የሚወስደው ክርስቶስ ግን በሞቱ ወደ ሕይወት መልሶናል። በዚህም የዲያብሎስን ጥበብ ሞኝነት እንደሆነ አሳይቶናል። ነፍሳትንም ሁሉ ወደ ራሱ ስቦ አቅርቧል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቤዛነቱ ሥራ ውጭ የፈጸማቸው ተግባራት ለአርአያነት ያከናወናቸው ናቸው። ለምሳሌ በዮርዳኖስ ከተጠመቀ በኋላ "ያመነ የተጠመቀ ይድናል" (ማር.፲፮፥፲፮) የሚል ሕግ መሥራቱ፤ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት

ከጾመ በኋላ "በምትጾሙበት ጊዜ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤ እነርሱ እንደ ጾሙ ይታዩ ዘንድ መልካቸውን ይለውጣሉና" (ማቴ.፮፥፲፮) ብሎ ማስተማሩ፣ ቀን እያስተማረ ውሎ ሌሊት በደብረ ዘይት እየጸለየ በማደር አርአያ ከሆነ በኋላ "ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ" (ማቴ.፳፮፥፵፩) ብሎ ማሳሰቡ በመጨረሻም የሐዋርያትን እግር አጥቦ እኔ እንዳደረግሁላችሁ እናንተም ለሌሎች እንዲሁ አድርጉ ብሎ ትሕትናን ማስተማሩ የጌታችን ወደዚህ ምድር መምጣት ከቤዛነት በተጨማሪ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን አርአያ ሊሆነን መሆኑን የሚያስገነዝበን ነው። "እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና" እንዲል። (ዮሐ.፲፫፥፲፭)

እግዚአብሔር እኛን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረን ስሙን ቀድሰን ክብሩን ወርሰን ለዘለዓለም እንድንኖር ነበር። ነገር ግን ለመኖር የተፈጠርነው እኛ የተሰጠንን ነፃ ፈቃዳችንን ያለአግባብ ተጠቅመን ከሕይወት ሞትን፣ ከክብር ውርደትን፣ ከደስታ ኀዘንን መረጥን፤ ከገነት ተባርረን ወደ ሲኦል ስንወርድ እግዚአብሔር የእኛን ዕዳና በደል በራሱ ላይ አኑሮ ለኛ የሚገባንን የሞት ፍርድ ተቀብሎ እኛን ወደ ቀደመው ክብራችን ሊመልሰን የእኛን ሥጋ ተዋሕዶ ተወለደ። የሞተውም ይህንኑ ዓላማ ለመፈጸም ነው እንጂ በድንገት አሊያም በሌሎች አስገዳጅነት አይደለም። ይህንን ምሥጢር በስፋትና በጥልቀት ያስተማረው ሶርያዊው የነገረ መለኮት ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬምም በዕለተ ዓርብ ውዳሴ ማርያም ላይ "ሰውን የሚወድ እርሱ ወደ እርሱ አቀረበን ክብር ምስጋና ያለው እርሱ የእኛን ሞት ተቀብሎ የእርሱን ሕይወት ለእኛ ሰጠን" ብሏል።

አባታችን አዳም እግዚአብሔር "ዕፀ በለስን እንዳትበላ" ብሎ የሰጠውን ትእዛዝ በማፍረሱ ደዌ ሥጋ ላይ ደዌ ነፍስን፣ ሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስን፣ ርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሃነመ እሳትን እንደፈረደበት የሚታወቅ ነው። ይህ ፍርድ ደግሞ ከአዳምና ከሔዋን በዘር በሩካቤ ለተወለዱ ሁሉ ስለ ደረሰ ወልደ እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም ተወልዶ በሞቱ ሞትን ደምስሶ፣ መቃብርና ሲኦልን ድል ነሥቶ እስካዳነን ጊዜ ድረስ ሁላችንም በዚህ ፍርድ ውስጥ እንደ ነበርን ይታወቃል። በኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ድኅነትም ስንል ከዚህ ሁሉ ርግማንና ፍርድ ነፃ መውጣትን ነው። ቅዱስ ኤፍሬምም "ከእኛ ርግማንን አጠፋልን፣ በመካከላችንም ሆኖ በመስቀሉ አስታረቀን በልዩ ትንሣኤውም ሰውን ዳግመኛ ወደ ገነት መለሰው" ያለው በወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን ያገኘነውን ድኅነት ጠቅልሎ ለመናገር ነው።

## ማጠቃለያ

ክርስቶስ ከሁሉ ከፍ ያለ ሁሉን ፈጥሮ የሚገዛ እርሱ ብቻ አምላክ መሆኑን ለማስተማር በባሕር ላይ እንደ የብስ እየተራመደ፣ ማዕበሉንና ነፋሱን እየገሠጸ፣ ውኃውን ወደ ወይን እየቀየረ፣ ኮረብቶችን እንደጠቦት እያስዘለለ፣ ድንጋዮች አፍ አውጥተው እንዲናገሩና አምላክነቱን እንዲመሰክሩ እያደረገ ሁሉን ወደራሱ ስቧል። ይህም የነገረ መስቀሉ አካል ነው። ምክንያቱም ክርስቶስ ይህን በማድረጉ አይሁድ ሰንበትን ሻረ ብለው ከሰውታል። ኋላም ለሞትና ለመከራ ያደረሱት ሌላ በደል ተገኝቶበት ሳይሆን እነዚህንና መሰል ድንቅ ድንቅ ሥራዎችን ስለሠራ ብቻ ነው።

እንዲሁ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ዕርቃኑን በተሰቀለበት ቀን ቀድሞ አማልክት ተብለው ይመለኩ የነበሩት ብርሃናውያኑ ፍጥረታት ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት የአምላካቸውን ዕርቃን ለመሸፈን ብርሃናቸውን ከልክለው የክርስቶስን አምላክነት በመናገራቸው አስቀድሞ ባለማወቅ እነዚህን ፍጥረታት ማለትም ፀሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ያመልኩ የነበሩ አሕዛብ አምላክ እርሱ ብቻ መሆኑን አምነው ወደ ክርስቶስ ቀርበዋልና ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ አለ። ስለዚህ ጌታ በዕፀ መስቀል ላይ የተሰቀለው ሞትን በሞቱ ገድሎ ዲያብሎስንም አስሮ የዲያብሎስን ምርኮ ለመመለስ መሆኑን እናምናለን። (ሉቃ.፲፩፥፳፪) እግዚአብሔር አምላካችን ከበረከተ ስቅለቱና ከበረከተ ትንሣኤው ያድለን አሜን።

# አቡነ ዮሐንስ ዘውራ ኢየሱስ

ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን



አቡነ ዮሐንስ ዘውራ ኢየሱስ

## ትውልድ

ጻድቁ አቡነ ዮሐንስ የአባታቸው ስም የማነ ብርሃን የእናታቸው ስም ሐመረ ወርቅ ይባላል። የተወለዱበት ቦታ አክሱም ጽዮን ነው። እናቱን ሐመረ ወርቅን ያለ ፈቃዷ ለአንድ ሀገረ ገዥ ሊያጋቧት ሲሉ የአባታችን የጻድቁን የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን እና የሌሎችን ቅዱሳን መቃብር ሳልሳለም አላገባም። ፍቀዱልኝና ተሳልሜ እመጣለሁ አለቻቸው። ይህን ጊዜም ከብዙ ሠራዊትና ከብዙ ገንዘብ ጋር ሰደዷት።

ቅድስት ሐመረ ወርቅ ደብረ ሊባኖስ የእመቤታችን የሥጋዋ ፍልሰት በሚከበርባት በነሐሴ ፲፮ ቀን ደረሰች። በዚያችም ሌሊት አባታችን ተክለ ሃይማኖትን በሕልሟ አየችው። የብርሃን ምሰሶም ከፊቷ አየች። ጻድቁም ይህ የብርሃን ምሰሶ ለአንቺና ለባለቤትሽ ለየማነ ብርሃን ነው አላት። ይህንም በገዳሙ ሱባኤ የገቡ መነኰሳት ለሰባት ተከታታይ ቀናት ያህል አዩ። ያዩትንም ለገዳሙ አበ ምኔት ለአባ ዳንኤል ነገሩት። እርሱም እኔም እንደናንተ አይቻለሁ አላቸው።

የአባቱ የየማነ ብርሃን ቤተሰቦችም እንዲሁ ደጋግና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ለተራብ የሚያበሉ፣ ለተጠማ የሚያጠጡ ነበሩ፣ በመጋቢት ሃያ ሰባት ቀን እመቤታችን ተገለጸችላቸውና ከልጃችሁ ከየማነ ብርሃን የብዙዎች አባት የሚሆን ደግ ልጅ ታገኛላችሁ ከጻድቁ ከተክለ ሃይማኖት በቀር የሚበልጠው የለም እናቱ ሐመረ ወርቅም በደብረ ሊባኖስ ገዳም ትገኛለች አሏቸው። ስለዚህ የየማነ ብርሃን እናትና አባት ከልጃቸው ከየማነ ብርሃን ጋር በምልክት ይፈልጓት ዘንድ ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄዱ።

የገዳሙ አበ ምኔት አባ ዳንኤልም ለነሐሴ ሃያ አራት ለጻድቁ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት በዓል ከአራቱም ማዕዘን የተሰበሰቡትን ስማችሁን ጽፋችሁ አምጡ አሏቸው። የሁሉንም ስም ሰብስበው ከጸለዩበት በኋላ የማነ ብርሃን እና ሐመረ ወርቅ በተክሊል እንዲጋቡ ነገሯቸው። ሐመረ ወርቅም ፈቃዳችሁ ፈቃዴ ነው ነገር ግን እናትና አባቴ ለማያውቁት ሰው ሚስት እሆን ዘንድ እናትና አባቴ አልፈቀዱልኝም አለቻቸው። አባ ዳንኤልና መነኰሳቱም ሐመረ ወርቅ ሆይ ክርስቶስ መረጠሽ፤ እመቤታችን ድንግል ማርያም ለየማነ ብርሃን ሚስት ትሆኚ ዘንድ አጨችሽ፤ እሺ በዪ አሏት። በዚህ ጊዜ እርሷም ፈቃደኛ ሆነች። በዚህም ዕለት በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ተጋቡ። ሥርዐቱ ከተፈጸመ በኋላ በጾምና በጸሎት ተወስነው ለሁለት ሳምንት በደብረ ሊባኖስ ተቀመጡ።

ከዚህ በኋላ ወደ ትውልድ ቦታቸው ወደ አክሱም ተመለሱ። በአክሱምም እንግዳ እየተቀበሉ፣ ለተራብ እያበሉ በመልካም ምግባር ሲኖሩ ነሐሴ ሃያ አራት ጻድቁ አባት ዮሐንስ ተፀነሰ፤ ግንቦት ሃያ አራት ቀንም ተወለደ፤ ስሙንም ዮሐንስ አሉት ትርጓሜውም ፍጹም ደስታ ማለት ነው።

## ዕድገትና ትምህርት

እናት አባቱ ቅዱሳት መጻሕፍትን፣ የቤተ መንግሥትንም ሥርዐት እያስተማሩ አሳደጉት። ዮሐንስም ለአባቱ የማነ ብርሃንና ለእናቱ ሐመረ ወርቅ በነገህም በሠርክም ይታዘዝ ነበር። በተወለደ በሰባት ዓመቱም ይህን ኃላፊውን ዓለም ናቀ። ኀልፈት ውላጤ ከሚስማማው ዓለም ኀልፈት ውላጤ የማይስማማውን ሰማያዊውን ዓለም መረጠ። የተክለ ሃይማኖት ሁለተኛ ልጅ ወደሆነው ጻጋ ኢየሱስ ሄደ። በዚያም ከጻጋ ኢየሱስ ጋር ለአምስት ዓመት ያህል ቆየ። ዐሥራ ሁለት ዓመት ሲሞላውም የምንኵስናን ሥርዐት በጻጋ ኢየሱስ ተቀበለ።

## የአገልግሎት ሁኔታ

ገና በዐሥራ ሁለት ዓመቱ የመነኰሰው ተጋዳይ አባት በዋልድባ ገዳም ገባ። በዚህም መነኰሳቱ በመዓልትም በሌሊትም ያገለግለው ዘንድ በሥጋው ቁስል ሁለንተናው የተላና የተበላሸ በጸባዩም እጅግ የከፋ ሰው ርዳው ብለው ሰጡት። ያም መነኵሴ ይረግመዋል፤ የሚማታበት ጊዜም ነበር። ጻድቁ ዮሐንስ ግን ፈጽሞ ይደሰት ነበር። ሥራው የከፋ የዚያን መነኵሴ ፈቃድ በገዳሙ የሚኖሩትን የመነኰሳትንም ፈቃድ እጅግ ደስ እያለው ያገለግል ነበር። በየዕለቱ ሰባት መሥፈሪያ ይፈጭ ነበር። እንጨት ለቅሞ ሰባት ጎልማሶች የሚያመጡትን ያህል ያመጣ ነበር። በምድረ በዳም ቋርፍ ይምስ ነበር። ከሰንበት ዕለት በቀር እህል ውኃ አይቀምስም ነበር።

እንዲህ እያደረገ ሰባት ዓመት ኖረ፤ የአርድእትንም በረከት ተቀበለ። የጻድቁ ድንቅ ሥራ ከተገለጠ በኋላ በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። ከጌታ መቃብርም ተሳለመ። ከዚህ በኋላ ታቦተ ኢየሱስን፣ ታቦተ ኪዳነ ምሕረትንና ታቦተ ጽዮንን እየጠበቀ ሁለት መቶ ዓመት በዚያ የኖረ ሁለተኛው እንጦንስን አገኘው። በእመቤታችን ፈቃድ ለእርሱ እንድተሰጠው የተነገረው ይህ አባትም ሦስቱን ታቦቶች ሰጠው። አባ ዮሐንስም ይጠብቀው ከነበረው አባት የተቀበላቸውን ሦስት ታቦታት ተቀብሎ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ።

አባ ዮሐንስ ከኢየሩሳሌም ያመጣቸውን ታቦታት በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ እየተመራ ታቦተ ኢየሱስን በሜጫ ወረዳ አንድ ውሮ የሚባል ባላባት ተቀብሎ ቦታ ሰስለሰጠው በዚያ ተከለ። የገዳሙንም ስም በባላባቱ ስም ውራ ኢየሱስ ብሎ ሰየመው። ገዳሙንም አከበረ፣ ከፍ ከፍም አደረገ። ከዘጠኝ ዓመት በኋላ መልአኩ ቅዱስ ዑራኤል እየመራው ወደ ዘጌ መጣ፤ በእርሷም ታቦተ ኪዳነ ምሕረትን ተከለ። የገዳሙንም ስም ዑራ ኪዳነ ምሕረት ብሎ ሰየመ። ከዚያም በኋላ ታቦተ ጽዮንን በአዴት አካባቢ ተከለ። ከንጉሡ ከኢያሱ ጋር እየተወያየ የገዳማቱን ርስት ጉልት በማስፋፋት በጎ አገልግሎት ሲያገለግል ኖረ።

## ተአምር

ጻድቁ አባ ዮሐንስ በርካታ ተአምራትን አድርጓል ከብዙዎችም መካከል

፩. በዋልድባ ገዳም ሳለ በአንድ ወቅት ከባድ ሕመም ተነሥቶ አንድ የገዳሙ መነኵሴ ሞተ፣ ሰው ሁሉ ፈርቶ ሳለ አበ ምኔቱ ብቻውን ሊከፍን ሲሄድ እርሱም አብሮ ሄደ። አበ ምኔቱ እንዳይሄድ ቢከለክለው አባታችን ዮሐንስም በለመለሙ ከንፈሮቹ ስለት በሆነው አንደበቱ አንተ ስትሞት እኔ አልቀርም አለ። ያን ጊዜም ወደ ሞተው ቀረበ፤ አቀፈውም ደም የተነከረ ልብሱንም ያዘ፤ ያን ጊዜም የሞተውን እንደ ጴጥሮስ፣ እንደ ጳውሎስና እንደ ሐዋርያት በጥላው አስነሣው። ያ ሙቶ የነበረውም ከሞትሁ ዛሬ ሦስተኛ ቀኔ ነው አይቶ የጎበኘኝ አልነበረም፤ ዛሬ ግን የእግዚአብሔር ሰው የገዳማቱ ኮከብ የቅድስት ውራ ገዳም መነኰሳት አባት የማይጠልቅ ፀሐይ፣ የማይጠፋ ፋና፣ ወደ ሰባቱ ሰማዮች ወጥቶ ዐርጎ ከሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ጋር የሥላሴን ዙፋን የሚያጥን አባታችን ዮሐንስ በአቀፈኝ ጊዜ ነፍሴ ከሥጋዩ ፈጽማ ተዋሐደች በማለት በወቅቱ የተፈጸመውን ድንቅ ተአምርና ወደፊት አባ ዮሐንስ የውራ ገዳም አባት እንደሚሆንም ትንቢት ተናገረ።

፪. በንጉሥ ኢያሱ ዘመን በንጉሡ ጠላት ተነሥቶበት የንጉሡን የሠራዊት አለቃ አገኘውና የንጉሡን ጠላት

ድል ታደርጋለህ፤ ነገር ግን ንጉሡን ለኪዳነ ምሕረት ርስት እንዲሰጠኝ ጠይቅልኝ አለው:: እርሱም እሺ ብሎ ከሄደ በኋላ ጠላቶቹን ድል ነሥቶ ሲመለስ ረሳው በመንገድ ላይ ግን ፈረሱ ከወንዝ ዳር ተኝቶ ከሦስት ሰዓት በላይ እንቢ አለ:: ከወንዙ ዳር እያሉ ውኃ እንዲያጠጡት አገልጋዮቹን ጠየቃቸው በዚህ ጊዜ አባ ዮሐንስ ለምልክት ትሁንህ ብሎ በሰጠው ቅል አመጡለት፤ ቅሏን ሲመለከት ትዝ አለው በዚህ ጊዜ መልእክቱን ሊያደርስ ወደ ንጉሡ ሲመለስ ፈረሱ ተነሣለት::

፫. አንድ ሰው ጎሽ ሊገድል ፈልጎ ወደ ጫካ ሲሄድ አንድ ጎሽ አገኘችው:: እርሱ ከማየቱ በፊት ቀድማ አየችውና ከፈረሱ ላይ ጣለችው:: በዚህ ጊዜ በዮሐንስ አምላክ አምየሻለሁ እንዳትገድዪኝ ብሎ ተማጸናት:: እርሷም ተወችው:: እርሷ ከተወችው በኋላ ግን ሊገድላት ፈለገ፤ እርሷም እንደ እርሱ ሁሉ በዮሐንስ አምላክ ተማጽኘሃለሁ አለችው:: አልሰማትም ወግቶም ገደላት:: ምላሷን በክንዱ አስቀምጦ፣ ቀንዷን ይዞ ወደ አባ ዮሐንስ ሄደ:: ቀንዷን ለአባ ዮሐንስ ሰጥቶ ሊባረክ ሲል ምላሷ ከክንዱ ላይ ወደቀችና የአባ ዮሐንስ ጥላ አረፈባት:: በዚህ ጊዜ በሰው አንደበት ድምፅዋን አሰምታ ተናገረች:: በሕያው እግዚአብሔር እማጸንሃለሁ፤ ነቢዩ ዳዊት "በጽድቅ ገሥጸኝ፤ በምሕረትም ዝለፈኝ፤ የኃጢአተኛ ዘይትን ራሴን አልቀባም" (መዝ.፻፵፩፥፭) እንዳለ በግፍ የገደለኝን የዚህን ዐመፀኛ ሰው እጅ መንሻ አትቀበል አለችው::

አባታችንም ሰውየውን ይህ ነገር እውነት ነውን ብሎ ጠየቀው:: ገዳዩም እውነት ነው በማለት መለሰ:: በዚህ ጊዜ አንተ በእውነት ከእርሷ ታንሣለህን? ከእርሷ ብሰህ እንዴት ትበድላለህ? አለው ሰውየውም ጥፋቱን አመነ:: ከዚህ በኋላ በመስቀል አማተበ፣ ሥጋዋንም ተቆራርጦ ከወደቀበት ቦታ ሰብስቦ በስመ እግዚአብሔር አስነሣት፣

ጻድቁ አባ ዮሐንስ ሌሎች ድንቅ ድንቅ ተአምራትንም አድርጓል:: ከእነዚህም መካከል ደዌያቸው ልዩ ልዩ የሆነባቸው ብዙ በሽተኞች ወደ እርሱ እየተሰበሰቡ ከበሽታቸውና ከደዌያቸው ይፈውሳቸው ነበር::

## ቃል ኪዳን

አገልግሎቱን በሰላም ከፈጸመ በኋላ ከዚህ ዓለም የሚለይበት ጊዜ ሲደርስ ሕይወቱን ሁሉ ከአገለገለውና ቸርነት የባሕርዩ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጽኑዕ ቃል ኪዳን ተቀብሏል:: ቃል ኪዳኑም ዝክርህን የዘከረ፣ በዓልህን ያከበረ፤ ገድልህን የሰማ፣ ያሰማ፣ መልክህን ጸሎት አድርጎ የደገመ፣ እባብ አይነድፈውም፤ መብረቅ አይገድለውም፤ በነፍሱ እስከ ዐሥራ አምስት ትውልድ ድረስ ይማራል:: ከምትቀበርባት ውራ ኢየሱስ መብረቅ አይወርድም:: የሚል ነው::

## በዓለ ዕረፍት

አባ ዮሐንስ መልካም የሆነውን ተጋድሎ ሲፈጽም ከኖረ በኋላ በሰማንያ ዓመቱ ጥቅምት ሃያ ሁለት ቀን አርፎ በውራ ኢየሱስ ተቀብሯል:: የጻድቁ በረከት ይደርብን አሜን::

*(ምንጭ ገድለ አቡነ ዮሐንስ ዘውራ ኢየሱስ)*

# የጥያቄዎቻችሁ መልስ

የጥያቄዎቻችሁ
መልስ

*በቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን*



መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ

***ውድ አንባብያን በጥያቄዎቻችሁ መልስ ዐምዳችን ትንሣኤ ሙታንን በተመለከተ ጥያቄዎችን መሠረት አድርገን ምላሽ ይሰጡን ዘንድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል (በተለምዶ ብሥራተ ገብርኤል እየተባለ በሚጠራው) ቤተ ክርስቲያን ሰባኬ ወንጌል የሆኑትን መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየን ጋብዘናል። መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳንም መደበኛ መምህር ናቸው። ያነሣንላቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ ፈቃደኛ ሆነውልን ቆይታችንን እንዲህ አዘጋጅተነዋል፤ መልካም ንባብ።***

***፩ ሐመር፡-*** ትንሣኤ ማለት ምን ማለት ነው?

***መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ፡-*** ትንሣኤ ማለት "ተንሥአ" ካለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን መነሣት አነሣሥ የሚል ትርጉም ይኖረዋል። ዘርፍ ሲይይዝ ደግሞ ባለቤት ይኖረዋል ማለት ነው። ለምሳሌ፡- ትንሣኤ ክርስቶስ፣ ትንሣኤ ሥጋ፣ ትንሣኤ ልቡና፣ ወዘተ. ሲል የክርስቶስ ትንሣኤ፣ የሥጋ ትንሣኤ፣ የልቡና ትንሣኤ እየተባለ ባለቤቱን እየጨመረ ይፈታል። ከውደቀት ወይም ከሞት በኋላ ያለ ሕይወትን የሚገልጽ ነው።

***፪. ሐመር፡-*** ከአምስቱ አዕማደ ምሥጢር መካከል አንዱ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ነው። ምን ማለት ነው? ምንስ የምንማርበት ነው?

***መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ፡-*** አምስቱ አዕማደ ምሥጢር ለእኛ የእምነት መሠረት ወይም ዶግማ ብለን የምንጠራቸው ናቸው። ምሥጢረ ሥላሴ የሥላሴን አንድነት ሦስትነት፣ የስም፣ የግብር፣ የአካል፣ የኩነት ሦትነት፣ የባሕርይ፣ የአገዛዝ፣ የሥልጣን፣ የህልውና ወዘተ. አንድነት የምንማርበት በጠቅላላው ምሥጢረ እግዚአብሔርን ለሰው ልጆች የምንገልጥበት ነው። ሁለተኛው ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆኑን የምንማርበት ነው። ለትንሣኤውም መሠረት የሆነው ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ሰው መሆኑ ነው። ሦስተኛው ምሥጢረ ጥምቀት ሲሆን የሥላሴን ልጅነት ስለምናገኝበት ምሥጢር የምንማርበት ነው። አራተኛው ምሥጢረ ቊርባንም እንዲሁ ለድኅነታችን ስለተሰጠን ስለ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የምንማርበት ምሥጢር ነው። አምስተኛውና የመጨረሻው ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ደግሞ ስለ ሰው ልጆች ዳግም መነሣትና ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት የምንማርበት ምሥጢር ነው።

ሁለቱን ማለትም ምሥጢረ ሥላሴንና ምሥጢረ ሥጋዌን እናምንባቸዋለን፤ እንታመንባቸዋለን። ሌሎቹን ግን አምነን እንሳተፍባቸዋለን። ሞቱን በሚመስል ጥምቀቱ እንጠመቃለን። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "በሞቱ ከመሰልነውም በትንሣኤው እንመስለዋለን" (ሮሜ ፮፥፭) በማለት እንደገለጸልን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀን ልጆቹ ለመሆን ትንሣኤውን ተስፋ እያደረግን ጥምቀቱን እንሳተፋለን። በጥምቀታችን ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ስንል ትንሣኤ ሙታንን ተስፋ ማድረጋችንን የሚያስረዳ ነው።

ጌታችን ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር እንዳደረ እኛም ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ እንላለን፡፡ ይህ ማለት እኛም ሞተን፣ ፈርሰንና በስብሰን አንቀርም እያልን በጥምቀታችን ትንሣኤውን መስክረን እንነሣለን፡፡ ምሥጢረ ጥምቀት የወደፊቱን ተስፋ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን እንገልጽበታለን፡፡ ይህም ማለት በሁለቱ ምሥጢራት በምሥጢረ ሥላሴና በምሥጢረ ሥጋዌ እምነታችንን መስክረን በምሥጢረ ጥምቀት ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን እንገልጽበታለን፡፡

በምሥጢረ ቊርባን ሥጋውን ደሙን ተቀብለን የዚሁ የምሥጢረ ትንሣኤ ባለቤቶች ሆነን ዘለዓለማዊ ሕይወትን ገንዘብ እናደርጋለን፡፡ ምሥጢረ ቊርባንን አምነን በመሳተፍ እግዚአብሔር በእኛ ያድራል፤ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር እንኖራለን፡፡ ሐዲስ ኪዳን የምንለው "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም ከእርሱ እኖራለሁ፡፡" (ዮሐ.፮፥፶፯) የሚለውን የምንገነዘብበት ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ስንፈጽም እርሱ እንደተነሣ እኛም ሥጋውን በመብላታችን ሕያው እንደምንሆን አምነን ትንሣኤ ሙታንን ተስፋ አድርገን እንጠብቀዋለን፡፡

ከዚህ በመቀጠል የተስፋው ፍጻሜ የሆነው በመጨረሻ የሚፈጸም ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ነው፡፡ ይህ ከነባለቤቱ ከነዘርፉ የተገለጸ ነው ነው፡፡ ሙታን የሚባሉት ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ የተፈጠሩት ሦስቱ ባሕርያት ተለይተዋቸው ወደ ተፈጠሩበት አፈር የሚመለሱት ናቸው፡፡ ሰው ሞተ የሚባለው ሦስት ነገሮች ማለትም ነፋስ ውኃ እና እሳት ሲለዩት አፈር ብቻ ሲቀር፣ ነፍስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር ሄዳ ተፈርዶላት በገነት ስትኖር ወይም ተፈርዶባት ወደ ሲኦል ስትወርድ ነው፡፡ ሰው እሳት ሲለየው፣ ይቀዘቅዛል፤ በእኛ ቋንቋ በድን ሆነ እንለዋለን፡፡ ውኃ ሲለየው ደግሞ የደም ዝውውር ያቆማል፤ ነፋስ ሲለየው የሕይወት እስትንፋስ የምንለውን ነገር ያጣል፡፡ ስለዚህ በዚህ ሂደት አፈር ወደ አፈርነቱ ይመለሳል፡፡

በመጽሐፈ መክብብ "አፈር ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ ነፍስም ወደሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ በሥጋም በነበረበት ጊዜ መልካም ወይም ክፉ ቢሆን ስለሠራው ሁሉ መልስ ሳይሰጥ ፈጣሪህን አስብ" (መክ.፲፪፥፯) ተብሎ እንደተነገረ አፈር ወደ አፈርነቱ ይመለሳል፡፡ ስለዚህ ሞት ማለት የአፈር ወደ ነበረበት ምድር መመለስ ነው፡፡ እነዚህ ሙታን አካል ተነሥተው ከመቃብር በመነሣት በእግዚአብሔር ቀኝ ወይም በእግዚአብሔር ግራ የሚቆሙበት ጊዜ ትንሣኤ ሙታን ይባላል፡፡ እነዚህ ሙታን መቃብር ክፈቱልኝ፣ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይሉ አምላካቸውን ክርስቶስን መስለው ፈጣሪያቸውን ተከትለውና እርሱን የትንሣኤያቸው በኵር አድርገው የሚነሡት ትንሣኤ ትንሣኤ ሙታን ይባላል፡፡

**፫. *ሐመር፡-*** *ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከርሠ መቃብር ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት አደረ ይላልና ይህ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት እንዴት ተቆጥሮ ነው የሚሞላው?*

***መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ፡-*** ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት ተብሎ የሚቈጠረው ጌታችን የሞተው ዓርብ ነው፡፡ ስለዚህ ዓርብ አንድ ተብሎ ይቆጠራል፡፡ ዋናው ጉዳዩ ፱ ሰዓት መሞቱ፣ ፲፩ ሰዓት መቀበሩ አይደለም፡፡ የሞተው በዕለተ ዓርብ ስለሆነ ዓርብ ሌሊቱን ጭምር ቆጥሮ አንድ መዓልት አንድ ሌሊት ይባላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ዓርብ ጧት ቢወለድ፣ ከሰዓት በኋላም ቢወለድ ዓርብ ተወለደ ነው የሚባለውና የዓርብን ሌሊትም ጨምሮ አንድ ተብሎ ይቆጠራል፡፡ ይህን ሊቃውንት መዓልት ይስህቦ ለሌሊት ወሌሊት ይስህቦ ለመዓልት፤ ቀን ሌሊትን ይስበዋል፣ ሌሊትም ቀንን ይስበዋል" በማለት ይገልጹታል፡፡ ደግሞም ሌሊት የሌለው ቀን ቀን የሌለው ሌትም ሊኖር አይችልም፡፡

ስለዚህ ዓርብ ዘጠኝ ሰዓት "አጽነነ ርእሶ ወመጠወ ነፍሶ፤ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን ሰጠ" (ዮሐ.፲፱፥፴) ተብሎ በቅዱስ ወንጌል እንደተጻፈ ዓርብ አንድ ቅዳሜ ሁለት እሑድም የተነሣ ሌሊት ቢሆንም መዓልቱን ስቦ ሦስት ተብሎ ይቆጠራል፡፡ ዕለት ማለት የ፲፪ ሰዓት ብርሃንና የ፲፪ ሰዓት ጨለማ ያለው ነው፡፡ ዕለት ብሂል ዘያስተዛውጎሙ ለመዓልት ወለሌሊት፤ ዕለት ማለት መዓልትና ሌሊትን አንድ የሚያደርጋቸው ነው" (ምንጭ፡- ብሉይ ኪዳን ትርጓሜ) በማለት ሊቃውንቱ እንደሚነግሩን ሌሊትና መዓልትን አንድ ያደረገ ነው፡፡ ዋናው ሰዓት ሳይሆን ድርጊቱ የተፈጸመበትን ዕለት ስለሆነ ከዓርብ ጀምረን እስከ እሑድ ስንቆጥር ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት ይሆናል፡፡

ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦ እንደምናገኘውና ሊቃውንቱም በምሥጢር እንዳስረዱን ዮናስ ወደ ከርሠ አንበሪ የገባው ዓርብ በሠርክ ነው፡፡ ከከርሠ አንበሪ

የወጣው ደግሞ እሑድ ሌሊት ነው:: (ምንጭ:- ትንቢተ ዮናስ ትርጓሜ) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምልክት ያሳዩት ዘንድ ለጠየቁት ሰዎች "እስመ በከመ ነበረ ዮናስ ውስተ ከርሠ አንበሪ ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ ለያልየ ከማሁ ይነብር ወልደ እጓለ እመሕያው ውስተ ልበ ምድር ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ ለያልየ፤ ዮናስ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በዓሣ አንበሪ ሆድ እንደ ነበረ እንዲሁ የሰው ልጅም ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በምድር ልብ ውስጥ ይኖራልና" (ማቴ.፲፪፥፵-፵፩) በማለት እንደ መለሰላቸው ምሳሌው ሆኖ የቀረበው ዮናስ ዓርብ በሠርክ ወደ ከርሠ አንበሪ (ሆድ) ገብቶ እሑድ በሌሊት እንደ ወጣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በዘጠኝ ሰዓት ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው ለይቶ በ፲፩ ሰዓት ተቀብሮ እሑድ ሌሊት መነሣቱ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አደረ እያልን የምንናገረው ይህን ነው::

***፬. ሐመር:-*** ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤውን በመጀመሪያ የገለጸው ለሴቶች ነው:: ለምን?

***መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ:-*** ሞት በመጀመሪያ ወደ ሰው ልጅ የመጣው በሴቶች ነው:: የሞት መርዶ ኀዘን በሴቶች እንደመጣ ትንሣኤውም በእነርሱ በኩል እንደመጣ ለማስረዳት ነው:: እንደሚታወቀው ሔዋን ጆሮዋን ከፍታ አእምሮዋን አንቅታ የዲያብሎስን ምክር በመስማቷ ምክንያት ሞት ወደ ሰው ልጅ መጥቷል:: እንዲሁ እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ጆሮዋን ከፍታ፣ አእምሮዋን አንቅታ የመልአኩን የቅዱስ ገብርኤልን ምክር በመስማቷ ሕይወት ወደ ሰው ልጅ ገብቷል:: ይህንም ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም እመቤታችንን ባመሰገነበት ውዳሴው "ስለሔዋን የገነት ደጅ ተዘጋ ስለ ድንግል ማርያምም ዳግመኛ ተከፈተልን" (ውዳሴ ማርያም ዘሐሙስ) በማለት አስረድቶናል:: ስለዚህ ሞትም ሕይወትም የጀመረው በሴቶች ነው ለማለት ትንሣኤውን ለሴቶች ገለጠው::

ሕይወት የሚረጋገጠው ደግሞ በትንሣኤው ነው:: አምላክ እኛን ከሞት ወደ ሕይወት ሊያሸጋግረን ወደዚህ ዓለም መጣ፤ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞትን ድል አድርጎ ተነሥቶ እኛን ከሞት ወደ ሕይወት አሸጋገረን:: ስለዚህ ሞትና ኀዘን በሴቶች በኩል እንደመጣ ሁሉ ደስታና ሕይወት ያለበትን ይህን ምሥጢርም ለእነርሱ ገለጠው::

ሌላኛው ምክንያት ወደ መቃብሩ በመገሥገሥና በመመላለስ በፈቅሩ በመቃጠል ሴቶች የመጀመሪያውን ደረጃ ይዘው እናያለን:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁድ እጅ ከተያዘበት ሰዓት ጀምሮ ሁሉ ሸሽተዋል:: እኩሌቶቹ ቤት ዘግተው ተደብቀዋል፤ እኩሌቶቹም በየቦታው ሸሽተዋል:: ይህ ሁሉ ሲሆን ሴቶቹ ግን በቅዱስ ወንጌል "በሰንበትም ማታ ለእሑድ አጥቢያ ማርያም መግደላዊትና ሁለተኛዋ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ" (ማቴ.፳፰፥፩) ተብሎ እንደተጻፈ ጨለማውን ሳይፈሩ፣ ወደ መቃብሩ ሲገሠግሡ እናያቸዋለን:: ስለዚህ የፍቅራቸው ዋጋ የፍቅራቸው መገለጫ ይሆናቸው ዘንድ ትንሣኤውን ለሴቶቹ ገለጸው::

ወደ መቃብሩ የሚሄዱትም ሽቱ ለመቀባት አስበው ነበር:: እንዲህ ያለው ልማድ የአይሁድ ልማድ ነበር:: አይሁድ ሰው በሞተ በሦስተኛ ቀኑ እንዲሁም በሰባተኛ ቀኑ መቃብሩን እየከፈቱ ሽቱ ይቀቡ ነበር:: ዛሬ እኛ ወደ ጸሎትና ወደ ምጽዋት ቀይረን በሠልስት፣ በሰባት፣ በዐሥራ ሁለት ወዘተ. የምናከናውነው በዚያ ልማድ ነው:: ለፍቅሩ ከመሳሳታቸው የተነሣ ሽቱ ሊቀቡ በሌሊት ሲሄዱ መልአኩን አገኙት:: በዚህም ያልጠበቁትን ነገር አገኙ:: ያገኙትም ነገር እነርሱ መቃብሩን ሽቱ ለመቀባት ሲሄዱ ጌታችን ተነሥቷል፤ መልአኩ "እናንተስ አትፍሩ፤ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንደምትሹ አውቃለሁና:: በእዚህ የለም እርሱ እንደተናገረው ተነሥቷል፤ ነገር ግን ኑና ተቀብሮበት የነበረውን ቦታ እዩ::" (ማቴ.፳፰፥፮) በማለት ነገራቸው:: የተሰቀለው ሌላ የሞተው ሌላ የተነሣው ሌላ እንዳልሆነ ለማስረዳት "የተሰቀለውን እንደምትሹ አውቃለሁና እርሱ ግን በዚህ የለም ተነሥቷል" በማለት የሞተው የተነሣው የተሰቀለው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን አስረዳቸው:: ይህን ሊቃውንቱ "ወዝ ነገረ መልአክ ያኤምር ከመ ስቅለተ ክርስቶስ ትምክሕተ ሰማያውያን ወምድራውያን፤ ይህ የመልአኩ ነገር የክርስቶስ ስቅለት የሰማያውያንም የምድራውያንም ትምክህት እንደሆነ ያስረዳል" (ምንጭ:- ትርጓሜ ወንጌል) ብለው ገልጸውታል::

ሌላው ሊቃውንቱ በትርጓሜያቸው ሴቶች መልእክትን (የምሥራችን) ለሰው ሁሉ ለማዳረስ ፈጣኖች ናቸውና የትንሣኤው የምሥራች ለዓለም ሁሉ በፍጥነት ይዳረስ ዘንድ ነው ብለዋል:: ይህም ይታወቅ ዘንድ መልአኩ "ፈጥናችሁም ሂዱና ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤ እነሆ ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል፤ በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ

ለደቀ መዛሙርቱ ንገሯቸው፤ እነሆም ነገርኋችሁ" ብሎ እንደነገራቸው ፈጥነው እየሮጡ ሄደው ለደቀ መዛሙርቱ ነግረዋቸዋል። "በፍርሃትና በታላቅ ደስታም ከመቃብሩ ፈጥነው ሄዱ፤ ለደቀ መዛሙርቱም ይነግሯቸው ዘንድ ሮጡ" (ማቴ.፳፰፥፯-፰) እንዲል።

በአጠቃላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ፣ ሞት በሴቶች በኩል እንደመጣ ሕይወትም በሴቶች በኩል መምጣቱን ለማስረዳት፣ እነርሱም ለፍቅሩ ስለሚሳሱና የትንሣኤው ዜና በፍጥነት ለዓለሙ ሁሉ ይዳረስ ዘንድ ለሴቶች ገለጸው።

***፩. ሐመር፦*** ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ ትንሣኤውን የገለጸው ለሴቶች ሲሆን ግን ማርያምን ለምን አትንኪኝ አላት?

***መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ፦*** አትንኪኝ ያለበት በዋናነት ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች አሉ። እነርሱም፦

በመጀመሪያ ደረጃ አለማመኗ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ እንደሚሞት፣ እንደሚቀበር እንዲሁም ሙስና መቃብርን ድል አድርጎ እንደሚነሣ ደጋግሞ አስተምሮ ነበር። ይህን ትንሣኤ አምና ብትቀበል ኖሮ አትንኪኝ አይላትም ነበር። አለማመኗ የሚረጋገጠው ደግሞ ከመቃብሩ አጠገብ ስትደርስ፣ መቃብሩ ባዶ ሆኖ ስታገኘውና ራሱን ጌታንም ስታገኘው ምንም እንኳን እርሱ መሆኑን ባታውቅም "ጌታዬን አይሁድ ወስደውታል መሰለኝ፣ አንተም ወስደኸው እንደሆነ ንገረኝ" እያለች ስትናገር ነበር። ይህ የአይሁድ ሐሳብ ነው። እርሷ ቃሉን የሰማች፣ እሞታለሁ፤ እነሣለሁ፤ ብሎ ሲያስተምር አብራ የተማረች ናትና "ወስደውታል መሰለኝ፤ አንተም ወስደኸው ከሆነ ንገረኝ" እያለች ባልተናገረችም ነበር። ስለዚህ አትንኪኝ ያላት ገና ያላመነችበት ስለነበር ነው። ከጌታችን ጋር ለመኖር ማመን የግድ ነው። ሳላመኑት አጠገባቸው ሁኖም ይርቅባቸዋልና ይህን ለማስረዳት ነው።

በሁለተኛ ደረጃ ሥርዐት ሊሠራ ፈቃዱ ስለነበር ነው። ይህም ሥርዐት የማጥመቅ፣ ቀድሶ ሥጋ ወደሙን የመፈተትና ለምእመናን የማቀበል፣ በአጠቃላይ የክህነት አገልግሎትን የማከናወን ድርሻ ለወንዶች መሆኑ ነው። ይህም ይታወቅ ዘንድ ቶማስን "ጣትህን ወዲህ አምጣና እይ፤ እጅህንም አምጣና ወደ ጎኔ አግባ፤ እመን እንጂ ተጠራጣሪ አትሁን።" (ዮሐ.፳፥፳፯) ማለቱን እንመለከታለን። ባለማመን ሁለቱም እኩል ናቸው ነገር ግን ቶማስን "ዳሥሠኝ" ማለቱ ማርያምን ደግሞ "አትንኪኝ" ማለቱ የክህነት አገልግሎት ለወንዶች ብቻ የተሰጠ የአገልግሎት ድርሻ መሆኑን ለማስረዳት ነው።

ሥልጣነ ክህነትን ለወንዶች ብቻ ያደረገውም በሴቶች ያለ ልማድ ስላለ ነው። ይህ ልማድም በየወሩ የሚመጣ ደም (የወር አበባ)፣ እንዲሁ በወሊድ ጊዜ የሚኖሩ ሁኔታዎች ተጠቃሾች ናቸው። የወር አበባ በሚመጣ ጊዜ እንኳንስ ከቤተ መቅደስ ገብቶ መቀደስ ማስቀደስም አይቻልም። በወሊድ ጊዜም እንዲሁ ነው። አንዲት እናት ወንድ ብትወልድ እስከ አርባ ቀን ሴት ብትወልድ እስከ ሰማንያ ቀን ቤተ ክርስቲያን አትገባም። በዚህ ጊዜ ደግሞ ቅዳሴ መቋረጥ የለበትም። በዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች መድኃኔዓለም ክርስቶስ ክህነትን የሰጠው ለወንዶች እንጂ ለሴቶች አይደለም። የሚገርመው ግን ይህ ልማደ አንስት ልጆች የሚገኙበት መንገድ መሆኑ ነው። በዚህ ተፈጥሯዊ ማንነት የሚገኙት ልጆች ደግሞ ወንዶች ቢሆኑ ካህን ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ ሴቶች ራሳቸው ካህን መሆን ባይችሉም የክህነት ምንጭ በመሆን ታላቅ አገልግሎት ያከናውናሉ።

***፮. ሐመር፦*** ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማርያምን አትንኪኝ ስላላት ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ወይም በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ቦታ የላቸውም ወይም እኩል አይደሉም የሚል ጥያቄ ይነሣልና ይህ እንዴት ይታያል?

***መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ፦*** ይህ ማለት ሴቶች የበታች ናቸው ማለት አይደለም። ለምሳሌ፦ በአንድ አካል ውስጥ ብዙ ብልቶች አሉ። የየራሳቸውን የሥራ ድርሻ ይሠራሉ እንጂ አንዱ የሌላውን ካልሠራሁ ሊል አይችልም። ባለመሥራቱም የበታች ነው ሊባል አይችልም። ዐይን እንደ ዐይንነቱ ያያል እንጂ እንደ ጆሮ ባለመስማቱ የበታች ነው አይባልም። ጆሮም እንደ ጆሮነቱ ይሰማል እንጂ እንደ ዐይን ባለማየቱ፣ እንደ አፍንጫ ባለማሽተቱ የበታች ነው ሊባል አይችልም። በቤተ ክርስቲያን የሴትና የወንድ የአገልግሎት ድርሻም እንዲሁ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ለሁሉም ቦታ አላት። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤውን ለሴቶች ሲገልጥ ወንዶቹ የበታች ናቸው አልተባሉም። ወዳጁ ዮሐንስ ያውም እስከ መስቀል ድረስ ያልተለየው እያለ፣ የሐዋርያት አለቃ ቅዱስ

ጴጥሮስ እያለ ለሴቶች ሲገለጥ ወንዶች የበታች ናቸው እንዳልተባለ ሁሉ የክህነት አገልግሎት ደግሞ የወንዶች ብቻ ስለሆነ ሴቶች የበታች ናቸው አያስብላቸውም። በክህነት አገልግሎት አይሳተፉ እንጂ በቤተ ክርስቲያን የየራሳቸው ድርሻ እንዳላቸው መገንዝብ ያስፈልጋል። ለምሳሌ፡- በጸሎተ ቅዳሴ ይበል ካህን፣ ይበል ዲያቆን፤ ይበሉ ሕዝብ የሚል አለ። በዚህ ውስጥ ይበሉ ሕዝብ በሚለው ላይ ሕዝብ ሲባል የወንዶችም የሴቶችም ድምር ማለት እንጂ ወንዶቹ ብቻ አይደሉም። ስለዚህ የበታችነትን የሚያሳይ አይደለም። ይልቅ በቅንነት መመልከት ያስፈልጋል።

ዓለም የሴቶች እኩልነት እያለ ሴቶች የበታች ተደርገው እንደሚታዩ እና የበላይ መሆን እንዳለባቸው ያቀነቅናል። ይሁን እንጂ ዓለም ስላቀነቀነ የበላይ ሊሆኑ አይችሉም። ቤተ ክርስቲያን ወንዶች የበላይ ናቸው ብላ ሳታስተምር ዓለም ወንዶች የበላይ ሁነዋል ስላለም የበላይ ናቸው ማለት አይደለም። ሲጀመር ወንድና ሴት እኩል ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለውን ጥያቄ ማንሣትም ተገቢ አይደለም። ምክንያቱም ከተፈጥሮ ጋር በተያያዘ የየራሳቸው ድርሻ ቢኖራቸውም ሁለቱም አስፈላጊ ናቸው። ከላይም እንደተገለጸው ዐይንና ጆሮ የየራሳቸው የሥራ ድርሻ አላቸው፤ የየራሳቸውንም ሥራ ይሠራሉ እንጂ አንዱ በሌላው ሥራ ጣልቃ አይገባም፤ ልግባም ቢል አይችልም። የየራሳቸው ድርሻ ያላቸው አካላት መሆናቸውና አንዱ የሌላውን ማከናወን አለመቻላቸው ደግሞ የበላይና የበታች ናቸው የሚያስብላቸው አይደለም።

ከነገረ ድኅነት አንጻርም ስንመለከተው በወንዶች ያልተመለሰ በሴቶች ማለትም በእመቤታችን በቅደስት ድንግል ማርያም በኩል ተመልሷል። ይህ ሲኖር ሴቶች ከወንዶች የበላይ ናቸው አያስብላቸውም። እንዲሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ሲያድነን ወንዶች ከሴቶች የበላይ ናቸው አያስብላቸውም። በነገረ ድኅነት ሴቶችም ወንዶችም እጅግ የጎላ ድርሻ አላቸው። ስለዚህ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወንዶች ይበልጣሉ ሴቶች ያንሣሉ ብላ አስተምራ አታውቅም። ወደ ፊትም አታስተምርም።

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የወንዶችንና የሴቶችን እኩልነት የምታረጋግጠው ተጋድሏቸውን የፈጸሙ ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን ጽላት ቀርጻ፣ ገድል ጽፋ፣ ቤተ ክርስቲያን አንጻ፣ በስማቸው ዝክር ትዘክራለች፣ አማልዱን እያለች ትጸልያለች፣ በዓል ታከብርላቸዋለች። ጻድቁን አቡነ ተክለ ሃይማኖትን እንደምታከብር ሁሉ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራንም ታከብራለች። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን የምታከብረው ሰውነትን እንጂ ጾታን አይደለም። ሰው የሚባለው ደግሞ ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ የተፈጠረ ሴትም ወንድም ሁሉ እንጂ ወንድ ብቻ አይደለም።

***፮. ሐመር፡-*** ከላይ ከተገለጸው በመነሣት የሴቶች በቤተ ክርስቲያን የሚኖራቸው አገልግሎት እስከምን ድረስ ነው የማያገለግሉበትስ የተገደበ አገልግሎት አለ ወይ?

***መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ፡-*** ሴቶች የተከለከሉበት የአገልግሎት ድርሻ ማጥመቅ፣ ቀድሶ ማቍረብ፣ መባረክ፣ በዐውደ ምሕረት ወጥቶ መስበክ፣ ወዘተ. እነዚህን በመሳሰሉ የክህነት አገልግሎቶች ላይ አይሳተፉም። ከዚህ በቀር ከላይም እንደገለጽነው በማኅበር ጸሎት ይሰተፋሉ። በዚህ ጉባኤ ላይ ሴቶች ወጥተው አያስተምሩም እንጂ ተቀምጠው ይማራሉ። ጉባኤ በተዘረጋበት ጳጳሳት፣ ካህናት፣ ዲያቆናት በአጠቃላይ ከምእመናን በማዕረግ የሚበልጡ አካላት የሚገኙበት ነው። በዚህ ጊዜ ደግሞ ሴቶች ብቻ አይደሉም የተከለከሉት፤ ማንኛውም ሰው ተነሥቶ ሊያስተምር አይችልም። ሊያስተምሩ ፈቃድ ያላቸው፣ የተሾሙ መምህራን ያስተምራሉ እንጂ ማንኛውም ሰው አያስተምርም።

አገልግሎት ማለት ማስተማር ብቻ አይደለም ተቀምጦ የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማውም አገልጋይ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማርታና በማርያም ቤት በገባ ጊዜ ማርታና ማርያም ያከናወኑትን አገልግሎትና የትኛው የተሻለ እንደነበር ወንጌላዊው ሉቃስ ሲገልጽ ማርታ ምግብ በማብሰል ትደክም እንደነበር ማርያም ግን ከጌታ እግር ሥር ተቀምጣ ትምህርቱን ትከታተል እንደነበር በዚህም የማርያም አገልግሎት እንደተመሰገነላት አስረድቷል። (ሉቃ.፲፥፴፰-፵፪)

ሴቶች ከላይ ከዘረዘርናቸው የክህነት አገልግሎቶች በቀር በሌላው ሁሉ ይሳተፋሉ። ለምሳሌ በሰበካ ጉባኤ ይሳተፋሉ፤ በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ባሉ የአገልግሎት ክፍሎች ኃላፊ እየሆኑ ማገልገል ይችላሉ። ከምንም በላይ ግን ከጥንት ጀምሮ ሴቶቹ በራቸውን ከፍተው ማዕድ አዘጋጅተው ነቢያትን፣ ሐዋርያትን፣ ሊቃውንትን፣ መምህራንን፣ ወዘተ. እየተቀበሉ ያስተናገዱ በርካታ ሴቶች ነበሩ። ለምሳሌ፡- በኤልያስ ዘመን መበለቲቱ ኤልያስን ከነበረበት ጽኑ ረኀብ

የታደገችው፣ በሐዋርያትም ዘመን የሐዋርትን ምግብ በማዘጋጀት ያገለግሉ የነበሩ በርካታ ሴቶች ነበሩ፤ ዛሬም አሉ:: አገልግሎት ማለት ደግሞ ይህ ሁሉ ተደምሮ ነው:: አገልጋዮች ካልበሉ ሊያገለግሉ አይችሉም:: ስለዚህ አገልጋዮች በአግባቡ ያገለግሉ ዘንድ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ደግሞ ዐውደ ምሕረት ላይ ወጥተው ከሚያስተምሩት ከመምህራኑ እኩል በረከትን የሚያስገኝ አገልግሎት ነው::

በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን ሴቶች የሌሉበት አገልግሎት የላትም:: ለምሳሌ:- በዝክረ ቅዱሳን ማለትም ቅዱሳንን በምንዘክርበት በዓመታዊ በዓላትም ይሁን በወርኃዊ በዓላት ሴቶች አሉ:: የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በአግባቡ እንዲከናወን ለአገልጋዮቹ ሴቶች ምግባቸውን በማዘጋጀት ያስፈልጋሉ፤ ጥንቱንም ወንጌል የተዳረሰው በሐዋርያት ብቻ ሳይሆን ሐዋርያትን እየተከተሉ ለሐዋርያት ያገለግሉ በነበሩት ቅዱሳት አንስት ጭምር እንደሆነም መገንዘብ ያስፈልጋል::

***፰. ሐመር:-*** በመጨረሻ ከነገረ ትንሣኤው ጋር በተያያዘ ቀረ የሚሉት ሐሳብ ካለ ቢገልጹልን?

***መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ:-*** ያላነሣነው በዙ ነገር ይኖራል:: ምሥጢረ ትንሣኤን ያህል ሰፊ ሐሳብ እንዲህ በአንድ ጊዜ አንሥተን ልንጨርሰውም አንችልም:: ይሁን እንጂ ትንሣኤ ሙታን ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ በትንቢትም በምሳሌያዊ ትንቢትም የተነገረ ነው:: ይህ በትንቢትም ሆነ በምሳሌያዊ ትንቢት የተነገረው የጌታችን የመድኃኒታችንም የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤም የሙታን ትንሣኤም ነው:: የጌታችንን ትንሣኤ የሚመለከት ምሳሌያዊ ትንቢት ማለት "ዮናስ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በዓሣ አንበሪ ሆድ እንደ ነበረ እንዲሁ የሰው ልጅም ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በምድር ልብ ውስጥ ይኖራልና" (ማቴ.፲፪፥፵-፵፩) ተብሎ በዮናስ አንጻር የተነገረው ነው:: ቀጥተኛ ትንቢት ደግሞ ነቢየ አግዚአብሔር ዳዊት "እግዚአብሔር ይነሣ ጠላቶቹም ይበተኑ" (መዝ.፷፯፥፩) በማለት የተናገረውን የሚመስል ነው::

የሙታንንም ትንሣኤ በተመለከተ ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ "ሙታን ይነሣሉ፤ በመቃብርም ያሉ ይድናሉ::" (ኢሳ.፳፮፥፲፱) በማለት ቀጥተኛ በሆነ ትንቢት ሲናገር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ "እውነት እውነት እላችኋለሁ የስንዴ ቅንጣት በምድር ላይ ካልወደቀችና ካልሞተች ብቻዋን ትኖራለች፤ ከሞተች ግን ብዙ ፍሬን ታፈራለች" (ዮሐ.፲፪፥፳፬) በማለት ምሳሌያዊ በሆነ ትንቢት ተናግሯል::

ይህ የትንሣኤ ሙታን ጉዳይ በሐዲስ ኪዳን የትንሣኤያችን በኵር የሆነው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ በመነሣት የእኛን ተስፋ ትንሣኤ አለምልሞታል:: ሐዋርያትም ይህንኑ አምልተውና አስፍተው አስተምረውታል:: ለምሳሌ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፣ በክርስቶስም የሞቱት አስቀድመው ይነሣሉ:: (፩ተሰ.፬፥፲፮) በማለት የተናገረውን እንመለከታለን::

በአጠቃላይ በኵራችን ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ተነሣ፤ እኛም እርሱን መስለን፣ እርሱን ተከትለን እንነሣለን:: የእኛ ትንሣኤ ግን አማናዊው ትንሣኤ ይሆንልን ዘንድ አስቀድመን ትንሣኤ ልቡና መነሣት ያስፈልጋል:: ካልሆነ ትንሣኤያችን ለክብር ሳይሆን ለኀሳር ሊሆንብን ይችላል:: ይህን በተመለከተ ነቢየ እግዚአብሔር ዳንኤል "በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎቹ እኩሌቶቹ ለዘለዓለም ሕይወት እኩሌቶቹም ለእፍረትና ለዘለዓለም ጕስቁልና ይነሣሉ::" (ዳን.፲፪፥፪) በማለት የተመለከተውን ራእይ ጽፎልን እናገኛለን:: የክብር ትንሣኤ እንጂ የኀሳር ትንሣኤ ደግሞ ትንሣኤ ሊባል አይችልም:: ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት "ስለዚህ ዝንጉዎች በፍርድ፣ ኃጥአንም በጻድቃን ምክር አይቆሙም" (መዝ.፩፥፮) በማለት እንደተናገረው እግዚአብሔር በሚመጣበት በፍርድ ቀን እናንተ የአባቴ ቡሩካን ከሚላቸው ጻድቃን ጋር በቀኝ መቆም ስለማይችሉ መነሣታቸው ባይቀርም ትንሣኤያቸው ግን የኀሳር ስለሆነ እንደ ትንሣኤ አይቆጠርም:: ይህ እንዳይሆንና በቀኙ ከሚያቆማቸው ጋር ለመቆም እንድንበቃ ዛሬ ትንሣኤ ልቡና ተነሥተን በእግዚአብሔር ፈቃድ ተመላልሰን መኖር ያስፈልጋል:: ትንሣኤ ልቡናን ተነሥተን በመጨረሻዪቱ የፍርድ ቀን በቀኙ እንዲያቆመን የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት የቅዱሳን መላእክት ጥበቃ የቅዱሳን ሁሉ ምልጃና ጸሎት አይለየን አሜን::

***ሐመር:-*** ላነሣናቸው ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስለሰጡን በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን::

***መጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ:-*** እኔም አመሰግናለሁ::

# “መልካም ማድረግን አትርሱ” (ዕብ.፲፫፥፲፮)

## ክርስትና በማኅበራዊ ሕይወት

በዲ/ን ተስፋዬ ምትኩ

ኃይለ ቃሉን የተናገረው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ነው:: ሙሉ ቃሉን ስናነበው “መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና” ይላል:: (ዕብ.፲፫፥፲፮) ይህን የቅዱስ ጳውሎስን ሐሳብ ያብራሩት መተርጒማነ መጻሕፍት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም “ለነዳያን መመጽወትን አትተዉ እናንተ በመስጠት እነሱ በመቀበል አንድ መሆናችሁንም አትርሱ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና” ብለዋል:: (የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው ፲፱፻፵፰ ዓ.ም ገጽ ፬፻፸)

የመልካምነት መገለጫዎች ብዙ ናቸው:: በርግጥ እንደየ ሰዉ አመለካከት፣ እምነትና ባህልም ይለያያል:: ከዚህም የተነሣ ለአንዱ መልካም የሆነው ለሌላ ክፉ የሚሆንበት አጋጣሚም ብዙ ነው:: በዚህም መሠረት እንደ ክርስትና ግን ነገሮችን መልካምና ክፉ፣ ኃጢአትና ጽድቅ፣ ጥሩና መጥፎ፣ ክብርና ውርደት፣… ብለን የምንለየው ሕግጋተ እግዚአብሔርን መሠረት አድርገን እንጂ የሰዎችን ባህልና አስተሳሰብ ወይም ዕድገትና ትምህርት መሠረት በማደረግ አይደለም::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ሥጋዌው አንድ ሰው ወደ እርሱ ቀርቦ “መምህር ሆይ፥ የዘለዓለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ?” ብሎ በጠየቀው ጊዜ “ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ ነው፤ ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ” በማለት ነበር የመለሰለት:: (ማቴ.፲፱፥፲፮-፲፯)

ያም ሰው ጥያቄውን በዚያ ሳይቆም “ትእዛዛቱ የትኞቹ ናቸው?” በማለት ጠይቆት ነበር:: ጌታም፦ “አትግደል፥ አታመንዝር፥ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥ አባትህንና እናትህን አክብር፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ” በማለት ትእዛዛቱ እነማን እንደሆኑ ነግሮታል:: በመጨረሻም “ይህንማ ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ፥ ደግሞስ የሚጐድለኝ ምንድር ነው?” ብሎ በመጠየቁ ጌታም የመልካምነት የመጨረሻ ጥጉን ሲነግረው “ፍጹም ልትሆን ብትወድ፥ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ” አለው:: (ማቴ.፲፱፥፲፰-፳፩)

በርግጥ ንብረቱን ሁሉ ሸጦ ገንዘቡን ለድሆች መጽውቶ ዓለምንና አምሮቷን ሁሉ ጥሎ ክርስቶስን መከተል ለሁሉ የሚቻል አይደለም:: (ማቴ.፲፱፥፲፩) ይህም ሆኖ ግን ይህን ሕይወት ማለትም ዓለምንና ፍላጎቷን ትተው ገዳማዊ ሕይወትን በተግባር ኖረው ያሳዩን ጥቂቶች አይደሉም:: ለምሳሌ በብሉይ ኪዳን ነቢዩ ኤልሳዕ ይህን አድርጓል:: ኤልሳዕ በግብርና ሥራ የሚተዳደር ባለጸጋ ሰው ነበረ:: እግዚአብሔር በነቢዩ ኤልያስ አድሮ ለመንፈሳዊ ተልእኮ ሲጠራው ግን ያርስባቸው ከነበሩት በሬዎች ከፊሉን በእርሻው ጥሎ፣ ከፍፊሉንም አርዶ ለድሆች መግቦ እናቱንና አባቱን ተሰናብቶ በእግዚአብሔር ጥሪ መሠረት ወደ አገልግሎት ተሰማርቷል::

“የሣፋጥንም ልጅ ኤልሳዕን በአሥራ ሁለት ጥማድ በሬዎች ሲያርስ፥ እርሱም ከአሥራ ሁለተኛው ጋር ሆኖ አገኘው:: ኤልያስም ወደ እርሱ አልፎ መጐናጸፊያውን ጣለበት:: በሬዎቹንም ተወ፥ ከኤልያስም በኋላ ሮጦ አባቴንና እናቴን እስማቸው ዘንድ፥ እባክህ፥ ተወኝ፥ ከዚያም በኋላ እከተልሃለሁ አለው:: እርሱም፦ ሂድና ተመለስ ምን አድርጌልሃለሁ? አለው:: ከእርሱም ዘንድ ተመልሶ ሁለቱን በሬዎች ወስዶ አረዳቸው፥ ሥጋቸውንም በበሬዎቹ ዕቃ ቀቀለው፥ ለሕዝቡም ሰጣቸው፥ በሉም እርሱም ተነሥቶ ኤልያስን ተከትሎ ሄደ፥ ያገለግለውም ነበር” እንዲል:: (፩ኛ ነገ.፲፱፥፲፱-፳፩)

በሐዲስ ኪዳንም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን ከንቱነት የዘለዓለም ሕይወትን ምንነት በነገራቸው ጊዜ መተዳዳሪያ ሥራቸውን፣ ሹመታቸውንና ሥልጣናቸውን፣ ሀብታቸውንና ንብረታቸውን፣ ሁሉ ጥለው የተከተሉ ብዙዎች ናቸው:: ከእነዚህም መካከል ጌታን የተከተሉ ዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ተጠቃሽ ናቸው:: ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ሐዋርያትን ሁሉ ወክሎ "እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ፤ እንኪያስ ምን እናገኝ ይሆን?" ብሎ ጌታውን የጠየቀው:: (ማቴ.፲፱፥፳፯)

ዘኬዎስ የተባለው ባለጸጋም ጌታን ወደ ቤቱ ጋብዞ ከሀብቱ እኩሌታውን ለድሆች ለመስጠት ቃል ገብቶለታል:: "ዘኬዎስም ጌታ ሆይ፥ ካለኝ ሁሉ እኵሌታውን ለድሆች እሰጣለሁ፤ ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደ ሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ አለው" እንዲል:: (ሉቃ.፲፱፥፰)

ሰው ከሀብት ከንብረቱ እኵሌታውን ከፍሎ ለድሆች መስጠት ለጥቂቶች እንጂ ለሁሉ የተሰጠ አይደለም:: ይሁን እንጂ ካለው ቀንሶ ለድሆች ማካፍል ማለትም ቁርሶ ማጉረስ፣ ቀዶ ማልበስና የመሳሰሉትን መልካም ምግባራት መፈጸም የምእመናን ሁሉ መንፈሳዊ ግዴታዎች፣ የመልካም ክርስቲያናዊ ሕይወትም መገለጫዎች ናቸው:: ይህ ስለሆነም ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻ ፍርድ ቀን ሊሆን ያለውን በተናገረበት ትምህርቱ በቀኙ ለሚቆሙት ጻድቃን "እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ:: ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና" እንደሚላቸው የነገረን:: ጻድቃን ደግሞ ትሕትና ልማዳቸው ስለሆነ መልካም ነገር ሠርተው አልሠራንም ይላሉና፤ ይህን ሲሰሙ "ጌታ ሆይ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ? እንግዳ ሆነህ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ? ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን?" ብለው ይጠይቃሉ:: እርሱም መልሶ "እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት" ይላቸዋል:: ኃጥአንን ደግሞ "ተርቤ፣ ተጠምቼ፣ ታርዤ፣ ታሥሬ ታምሜ ከእኔ ጋር አልነበራችሁምና ከእኔ ወግዱ" ይላቸዋል:: ኃጥአን ግን ጥፋታቸውን ከማመን ይልቅ ለስንፍናቸው ምክንያ ማቅረብ ልማዳቸው ነውና "መቼ አገኝተንህ አላደረግንልህም" ብለው ይከራከሩታል:: ጌታ ደግሞ "እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም" ብሎ ይመልስላቸዋል:: (ማቴ.፳፭፥፴፬-፵፭)

ከዚህ ሁሉ የምንገነዘበው ድሆችን ማሰብ፣ ችግራቸውን መካፈል፣ ከደስታችንም ተካፋዮች እንዲሆኑ መጋበዝ የምእመናን ሁሉ መንፈሳዊ ግዴታቸው መሆኑን ነው:: ክርስቲያናዊ ሕይወት ደግሞ ዕለት ዕለት የምንኖረው ነውና ድሆችን ማሰብም የሁል ጊዜ ተግባራችን ሊሆን ይገባል:: በተለይም የጻድቃንን፣ የሰማዕታትን፣ የቅዱሳን መላእክትንም በዓላቸውን በምናደርግበት ዕለት ከማንም አስቀድመን ድሆችን በቤታችን ልንጋብዛቸው ይገባል:: በዓሉን በምናከብርለት ቅዱስም ስም ድሆችን ቆርሰን ማጉረስ ቀደን ማልበስ ይገባል:: በዚህም "ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፥ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል፤ ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ አንዲት ጽዋ ቀዝቃዛ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙሬ ስም የሚያጠጣ፥ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋው አይጠፋበትም::" ተብሎ እንደተጻፈልን የምንዘክርለት ቅዱስ ያገኘውን ጸጋና በረከት እንወርሰለን:: (ማቴ.፲፥፵፩-፵፪) አስተውሉ በዓሉን የምናከብርለት ቅዱስ ለዚህ ክብር የበቃው በብዙ ተጋድሎ ሲሆን እኛ ደግሞ በቅዱሱ ስም ቁራሽ እንጀራ፣ ጥርኝ ውኃ፣ ድቃቂ ሳንቲም እላፊ ጨርቅ በመስጠት ብቻ ቅዱሱ በብዙ ተጋድሎ ያገኘውን ጸጋና በረከት ተካፋይ እንሆናለን::

ከሁሉ በላይ ደግሞ የሕይወት መሠረት፣ የቅድስና ምንጭ፣ የጸጋም ሁሉ ባለቤት የሆነውን የክርስቶስን በዓል ስናከብር በተለይም እርሱ ከዘለዓለማዊ ረኀብና ጥም የሚያድነንን ሥጋውንና ደሙን የሰጠበትን ሞትንም ድል አድርጎ የተነሣበትን በዓለ ትንሣኤን ስናክብር ድሆች ከእኛ ጋር

አብረው የደስታችን ተካፋይ እንዲሆኑ መጋበዝ ክርስቲያናዊ ግዴታችን መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ ያለበለዚያ በዓሉን በማክበራችን ክርስቶስን አስደስተናል ማለት አንችልም፡፡ በእውነቱ ከሆነ ከልጆቹ መካከል ግማሾቹ ተርበው ሲያለቅሱ ሌሎች ደግሞ ጠግበው ሲጨፍሩ፣ የተራቡትን ትቶ ከጠገቡት ጋር አብሮ የሚጨፍር አባት ይኖራልን? በርግጥ ይኖር ይሆናል፡፡ የእኛ አባት ክርስቶስ ግን እንዲህ ያለ ርኅራኄ የሌለው አባት አይደለምና ድሆች ሲራቡ ያዝናል፡፡ የሚያዝነው ግን እንደ ድሃ አባት የሚሰጠውን አጥቶ አይደለም፤ እኛ እንድንጸድቅበት ያዘጋጀልንን ዕድል መጠቀም ባለመቻላችን ነው እንጂ፡፡ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት "ለድሃ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል፥ በጎነቱንም መልሶ ይከፍለዋል" በማለት የገለጸው ይህንን እውነት ነው፡፡ (መዝ.፲፰፥፲፯)

እንደሚታወቀው "ብድር" ያጣና የተቸገረ ሰው ለጊዜአዊ ችግር ማለፊያ ብሎ ካለው ሰው የሚቀበለው ገንዘብ ነው እንጂ የሚቀር አይደለም፡፡ ምን አልባት አበዳሪውም ለጊዜው የሚያበድረው ስላለው እንጂ ስለ ተረፈው ላይሆን ይችላል፡፡ ባለው ጊዜ ያበደረው ገንዘብ በእጁ ያለው ገንዘብ በሚያልቅበት ጊዜ ስለ ሚደርስለት ትልቅ ተስፋ ይኖረዋል፡፡ በርግጥ ለሰው ያበደርነው በችግራችን ጊዜ ላይደርስልን ይችል ይሆናል፤ ተበዳሪ መልሶ የመክፈል አቅምም ሊያጣ ይችል ይሆናል፡፡ አበዳሪው ግን ያለ ተያዥ ስለማያበድር በተያገዡ በኩል ገንዘቡን ያገኛል፡፡ ለመሆኑ ተያዡስ ማን ነው ለገባለት ቃሉ ታምኖ በቸገረን ጊዜ የገባልንን ቃል መፈጸም ይቻለው ይሆን? ለድሃ ለምናበድረው ገንዘብ (ለምንመጸውተው ምጽዋት) ግን አስተማማኝ ተያዥ አለን፡፡

ይህም ተያዥ የዕለት ጉርስ አጥተን በተራብን ጊዜ ወይም የዓመት ልብስ አጥተን ስንራቆት ከብዙ ደጅ ጥናት በኋላ የሚደርስልን ምድራዊ ባልንጀራ አይደለም፤ ስለ እኛ የተራበ፣ ስለ እኛ የተጠማ፣ ስለ እኛ ርቃኑን የተሰቀለ፣ እስከ መስቀል ሞት፣ እስከ መቃብርም ድረስ ዋጋ የከፈለልን፣ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ፣ "ብሉ፤ ጠጡ፤ ከዘለዓለም ረኀብም ዳኑ፤" ያለን፣ በጸጋው ርቃናችንን የሸፈነልን፣ በሞቱ ሞታችንን ድል የነሣልን፣ በትንሣኤውም ትንሣኤያችንን ያወጀልን፣ ዕድሜ ዘመናችንን ሙሉ ከፍለን የማንጨርሰውን የበደላችንን ዕዳ ከፍሎ ከፍጹም ባርነት ነፃ ያወጣን፣ ሳይገባን ልጅነትን የሰጠን፣ ከገቡ መውጣት ካገኙም ማጣት የሌለበትን ፍጹሙን ተድላ መንግሥቱን ሊያወርሰን የታመነ የማያልቅበት ፍጹም ባለጸጋ እግዚአብሔር አምላካችን ነው፡፡

ስለዚህ ይህን ታላቅ የአባትነት ውለታ በምንዘክርበት በበዓለ ትንሣኤ ክርስቶስ እንደራራልን ለድሆች መራራት፣ ከችግራችን ነፃ እንዳወጣንም የድሆችን ችግር መጋራት፣ ደስታችንን እንዳበዛልንም ድሆችን ማስደሰት አይገባንምን ብቻችንን በልተን፣ ጠግበን፣ ለብሰንና አጊጠን ስንደሰት የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ የሌላቸውን ከዘነጋናቸው ግን ራስ ወዳዶች ሆነናል፡፡ "እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት" ያለውን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃልም ዘንግተናል፡፡ (ዮሐ.፲፭፥፲፪) ስለዚህም "ተርቤ አላበላችሁኝም፤ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝም፤ … ከእኔ ወግዱ" መባላችን አይቀርም፡፡

**ሰው ከሀብት ከንብረቱ እኵሌታውን ከፍሎ ለድሆች መስጠት ለጥቂቶች እንጂ ለሁሉ የተሰጠ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ካለው ቀንሶ ለድሆች ማካፈል ማለትም ቆርሶ ማጉረስ፣ ቀዶ ማልበስና የመሳሰሉትን መልካም ምግባራት መፈጸም የምእመናን ሁሉ መንፈሳዊ ግዴታዎች፣ የመልካም ክርስቲያናዊ ሕይወትም መገለጫዎች ናቸው፡፡**

ስለሆነም ምእመናን ሳይሳሳ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ከዘለዓለም ረኀብ ያዳነንን ጌታ ትንሣኤውን ስንዘክር ድሆችንና ጾም አዳሪዎችን እናት አባት የሞቱባቸውን ልጆችና ጠዋሪ ቀባሪ ያጡ አረጋውያንን ልናስባቸውና ደስታችንን ልናጋራቸው ይገባል፡፡ ያለበለዚያ ግን የክርስቶስን በዓል ያለ ክርስቶስ ብቻችንን እንደ ማክበር ይቆጣራል፡፡ ምክንያቱም የክርስቶስ ማደሪያዎች የሆኑትን ድሆችን አላገለገልንምና፡፡ በክርስቶስ በዓል ከክርስቶስ ተለይቶ ብቻ ከመዋል በላይ ብክነት የለም፡፡ ለዚህ መልካም ምሳሌ የምትሆነን ማርታ ነች፡፡

ማርታ ከዕታት አንድ ቀን ጌታ ቤቷ ውስጥ በመጣ ጊዜ እኅቷ ማርያም በጌታ እግር ሥር ቁጭ ብላ ስትማር እርሷ ግን እንግዳ መጣብኝ ብላ ምግብ ልትሠራ ትባክን እንደነበር ታሪኳ ይናገራል፡፡ የማርታ ነገር የሚያሳዝነው ምግበ ሥጋ ምግበ ነፍስን የፈጠረ፤ ለእስራኤል አርባ ዘመን ሙሉ መና የመገበ፣ ጥቂቱን እንጀራና ዓሣ አበርክቶ የአምስት ገበያ ሕዝብን የመገበ ጌታ በቤትዋ ሳለ ብቻዋን መባከኗ ነው፡፡ ዛሬም ብዙዎቻችን ድሆችን ወደ ቤታችን የማንጠራቸው፣ አቅማችን አይፈቅድልንም፣ የደገስነውም ለሁላችን አይበቃም በሚል ሥጋት ነው፡፡ የሚገርመው ግን እኛ ድሆችን ወደ ቤታችን ጠርተን ከእነርሱ ጋር አብረን ስንበላ አብረንም ስንጠጣ ከእነርሱ ጋር አብሮ ወደ ቤታችን ከሚገባው ክርስቶስ ጋር አብረን እንደምንበላ አብረንም እንደምንጠጣ ያለማስተዋላችን ነው፡፡ ታዲያ በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ የአምስት ገበያ ሕዝብ የመገበውን፣ ውኃውን ለውጦ ጣፋጭ የወይን ጠጅ አድርጎ የዶኪማስን ልብ ያሳረፈውን በአጠቃላይ ጥቂቱን ማብዛት ብቻ ሳይሆን የሌለውን እንዲኖር ማድረግ የሚቻለውን ጌታን ወደ ቤታችን ጠርተን ለመጋበዝ እንዴት እምነት አጣን? ማርታም የባከነችው ጥቂት እምነት አጥታ ነበር፤ ጌታም "ማርታ፥ የሚያስፈልገው ጥቂት ሆኖ ሳለ ስለምን ትባክኛለሽ" አላት፡፡ በእግሩ ሥር ቁጭ ብላ ቃሉን ትመገብ ስለነበረችው ስለ እኅቷ ስለ ማርያምም ሲናገር "ማርያም ግን መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም" ብሏል፡፡ (ሉቃ.፲፥፴፰-፵፪)

ዛሬም እንደ ማርታ ብኩን የሆንን ብዙዎች ነን፡፡ ለበዓሉ የሚያስፍልገንን ዶሮውን፣ በጉን፣ ቁርጡን፣ ጥብሱን፣ ማሩን፣ ጠጁን፣ ለማዘጋጀት ብዙ እንደክማለን፤ ልክ እንደማርታ፣ የሀበሻ ልብስ፣ የፈረንጅ ልበስ እያልን እንጨነቃለን፡፡ የበዓሉን ባለቤት ክርስቶስን ግን ሳንጋብዘው እንቀራለን፤ በዓሉ የማን እንደሆነ ከማን ጋርም ማክብር እንዳለብን፣ ማንን መጋበዝም እንደሚገባን አናውቅም፡፡ በየቤቱ በልቶ የጠገበውን ጠጥቶ የሰከረውን ጋብዘን አልበላ አልጠጣ በሚልበት ጊዜ ባይጣፍጥ ነው እንጂ ምግቡና መጠጡ ቢጣፍጠውማ ይበላልን ነበር በሚል ተጨማሪ ጭንቀት ውስጥ እንገባለን፡፡ ከዚህ በላይ ብክነት ምን አለ? በድሆች አድሮ "ራበኝ፤ ጠማኝ፤ አብሉኝ፤ አጠጡኝ" እያለ ያለውን በደጃችን የቆመውን ክርስቶስን ገፍተነዋልና፤ ሁሉ እያለን ባዶነት ይሰማናል፤ በደስታችንም ቀን በከንቱ እንጨነቃለን፡፡ የክርስቶስን በዓል ያለ ክርስቶስ ማክብር ማለት ይህ ነው፡፡ ማርታም የገጠማት ይህ ነበር፡፡ ለክርስቶስ የሚያስፍልገው ምን እንደሆነ ሳታውቅ፣ ክርስቶስን ለማስደሰት ትባክን ነበረና፤ አልፎ ተርፎም ለክርስቶስ የሚያስፍልገውን ዐውቃ ለክርስቶስ ልቧን የሰጠችውንና በእግሩ ሥር ቁጭ ብላ መማርን የመረጠችውን እኅቷንም ትቃወም ነበር፡፡ እንግዲህ እኛ ማርታን ሳይሆን ማርያምን እንሁን፤ ክርስቶስን ለማስደሰት ብዙ መጨነቅ ሳይሆን እርሱ የሰጠንን ጥቂቱን ከድሆች ጋር ተካፍሎ መብላት በቂ መሆኑን እንገንዘብ፡፡

# የፍስክ ብፌ

## ኪነ ጥበብ

*በደመላሽ ኃ/ማርያም*

ብዙ ተማሪ ሲተራመስበት የነበረው ትምህርት ቤት ተማሪዎቹን በሆዱ ከቶ ጭጭ ብሏል፡፡ እስከ መጨረሻው ክፍት ብሎ የነበረው በር የሚያስፈልገውን ያክል ተማሪ ከቶ ተዘግቷል፡፡ ከአርፋጅ ተማሪዎች ጋር ሲሯሯጡ የነበሩት ዩኒት ሊደርና ጥበቃዎች እፎይ ብለዋል፡፡ ጥበቃው አለሁ ለማለት ያህል ትልቁን የወታደር ከስክስ ጫማቸውን በከፊል ከውጭ አድርገው ጋደም ብለዋል፡፡ ለዕይነት ያህል የተማሪዎቹን ጫጫታ ለመርሳት በብዛት እሽ የምትል ሬዲዮናቸውን ከጆሯቸው አፋፍ አስቀምጠው ይሰማሉ፡፡ ዩኒት ሊደሩ የብዙ ሴትና ወንድ ተማሪዎችን መቀመጫ የቸበቸበች አርጩሜያቸውን ጥለው ጣታቸውን ለብዕር ሰጥተዋል፡፡ ቅጥር ግቢው ውስጥ በየክፍሉ ዕወቀትን ለማጋባት ከሚውተረተሩት መምህራን ድምፅ ውጪ ዝም ብሏል፡፡

ሰሙነ ሕማማት በመሆኑና ኮሮና ቫይረስም በጋራ አልያችሁ ስላለ የከተማው ሰው ራሱን ከችግር ለመከላከል ከቤቱ ከቷል፡፡ ገሚሱ ከበሽታ ሽሽት፤ ገሚሱ ሥጋውን እየጎሰመ ፈጣሪውን ይቅር በለኝ ብሎ በስግደትና በጾም ለመለመን፡፡ በዚህ መካከል ታዲያ እውነትም የቫይረሱን አደገኛነት እና ገዳይነት ካልተረዱ ወጣቶች ውጪ እምብዛም የሰው ትርምስ አይታይም፡፡

ከሥራ መልስ አንድ ሁለት ብለው የሚገቡትም ባለትዳሮች ደረስኩ ደረስኩ እያለ በመጣው የትንሣኤ ወጪ ‹‹ቀሪ ሒሳብዎት አነስተኛ ነው፡፡ እባክዎን ከቤት ከመውጣትዎ በፊት ትንሽ ገንዘብ ይያዙ›› ብሎ መልእክት የሚያስተላልፍ የመሰላቸውን የኪስ ቦርሳቸውን አኩርፈው ቤት ውለዋል፡፡ ኑሮው ጣሪያ በመንካቱ ገና ዶሮና በጉ ሳይገዛ በጤፍና በሽንኩርት የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ጎጆ ተፈትኗል፡፡ በዚህ ምክንያት “ሥጋ ድሮ ይበላ ነበር!” ብለን ለመተረክ እንዳንበቃ የሚሰጉም ጥቂቶች አልነበሩም፡፡

‹‹እኔ እምልህ ምነው ዛሬ በጊዜ ገባህ? አጣጮችህ በጠቅላላ ለሕማማቱ ገዳም ገቡ ወይስ መጨለጫችሁ ተዘጋ?›› አለች ወይዘሮ መሠረት ከሥራ ስትገባ ባሉዋ ያለወትሮው ቤቱ በጊዜ መግባቱ ገርሟት፡፡

‹‹እንዴ ምን ማለት ነው? አባወራ ቤቱ በጊዜ መግባት ነውር ሆነ እንዴ? ... ወይስ እናንተ የከተማ ሴቶች ባል በጊዜ ሲገባ ያስጠላችኋል? አይዞሽ ቢራ ቢራ የሚል ትንፋሼን ናፍቀሽ ከሆነ ትንሽ ቀን ታገሽኝ እንጂ ጨልጨልሽ እመጣለሁ››

‹‹አ አ!! ደግሞ በአልኮል የተሟሸ ትንፋሽ ምኑ ይናፍቃል ... ግዴታ ሆኖብኝ እንጂ አፍህን እዛው የጠጣህበት አስቀምጠህ ብትመጣ እንዴት በወደድኩህ ... ግን አይቻልም ደግሞ ተቀያይሮ የባሰ ቢመጣ ምን ይውጠኛል!››

‹‹አቤት አቤት በእኔ በባልሽ የተጋባብሽን ሱስ በቀጥታ ላለማውራት “ዓሳ በለው በለው” ትጫወቻለሽ ... ምን አለፋሽ ሚስቴ ... ከኔ ባልተናነሰ አንቺም እራስሽ የቢራ ሱስ አናውዞሻል››

‹‹እኔ ልጅት አይነካካኝም ... የማን ልጅ መሰልኩህ ... ጉሮሮዬን ከማንጎና ከብርቱካን ጁስ ውጪ ነክቶት እንደማያውቅ ታውቃለህ ... ምን ያደርጋል አንተን ጠጃም ባል ካገባው በኋላ ጁስ በሥዕል እንጂ በግብሩ አጣሁት፡፡››

‹‹እሺ የኢትፍሩት ብቸኛ ልጅ  ያለ ጁስ ምንም ሳይቀምስ ያደገ ቁንጅናን ነዋ በቢራ አየር የምበክለው ... ይቅርታ የኔ ሚስት ... አሁን ይልቅስ ደሞዜም እንደምታውቂው ገና የቅርጫውን እንኳን ሳልከፍል ብን ብሏል፡፡ ሁለት መቶ ብር ስጪኝና አባሪኝ?››

‹‹ይኸው የጠረጠርኩት መች ቀረ! ... ገብቶህ የአባወራነት ክብርን ናፍቀህ ሳይሆን ማጣት ጓደኛው አርጎህ በጊዜ እንዳስገባህ መች አጥቼው ... ለማንኛውም ለበዓል የምናወጣው ሁለታችንም መሰለኝ እንኳን ሁለት መቶ ብር ቤሳ ቤስቲን የለኝም! ... ደግሞስ ምን አለ አሁን እንኳን በሕማማቱ መጠጣት ቢቀርብህ ... ልጅ አይደለህ ምን አለ ትንሽ ብታሰተውል›› አለችው ነጠላዋን ከቁም ሳጥኗ አውጥታ ለመልበስ ሥራዋን ሳታቆም፡፡

"መቼ ጾሜ የማቀውን ነው ሚስቴ … ዛሬ ደርሰሽ ቄስ ልታደርጊኝ የምትሞክሪው?"

"ኧረ ባክህ አንተ ሰውዬ ቀዝቀዝ በል። እንዴ ነገረ ሥራህን እኮ ሲያዩት ገና የሃያ ዓመት ጎረምሳ ነው የምትመስለው፡ ፡ ትልቅነትህን አትዘንጋ እንጂ … ስስሙ ኦርቶዶክስ ነህ ግን ሕፃናት እንኳን ሊጾሙት የሚገባውን የአዋጅ ጾም አትጾምም።" አለች ምርር ብሏት ነጠላዋን እያራገፈች

"ያለመደብኝን ምን ሳርግ ሚስቴ"

"ምን ማለት ነው። በፊትስ ማስተዋል አቅቶህ ቤተሰቦችህም ስላላስተማሩህ ነው እንበል። ዛሬ ግን የንስሐ አባታችን የሚጨቀጭቁህ አይበቃም። እስከ መቼ ቸልተኝነት። ሞት እኮ ቀጠሮ አይሰጥም፤ እራስን በንስሓ ዝግጁ አድርጎ መጠበቅ አይሻልም"

‹‹ይልቅ እሱን ተዉና ብሩን ስጪኝ ስሞትልሽ ሚስቴ! … በሜሮኔ ሞት … አንገቱ ላይ ሰንሰለት እንደተደረገበት ውሻ እጥፍጥፍ ብዬ ሳመሽ አላሳዝንሽም?››

‹‹አታሳዝነኝም! … እንደውም ባሌ ካገባሁት ከስንት ዓመት በኋላ ቤቱ ስላመሸልኝ ደስ ብሎኛል … በዛ ላይ በሕማማት … በዛውም ለአፍህ እና ለጨጓራህ ዕረፍት ስጣቸው ››

‹‹ነው!››

‹‹አዎ!››

‹‹መጨካከን ተጀመረ ማለት ነው?!››

‹‹አዎ አልኩህ አታስፈራራኝ … እንደውም ሜሪዬ ትንሽ ብር እፈልጋለሁ ብላኝ ነበር … ትሰጣታለህ››

‹‹እቤት! ከየት? በአሁን ሰዓት የብብቴን ጸጉር ንጭ ካልሆነ በስተቀር ገንዘብ አምጣ የሚለኝ ደሜን ያፈላዋል … እኔ የምለው እስከአሁን ግን የት ሄዳ ነው ያላየኋት?›› አለ የቤቱን ሁሉንም አቅጣጫ በዐይኑ እየቃኘ የልጁን አለመኖር አስተውሎ።

‹‹ሆ! ሆ! እስቲ አታስቀኝ አንተ … ስለልጅህ ተጨንቀህ የት የምታውቀውን እና ነው የት አመሸች የምትለኝ? … ነው ወይስ ማጣት ከቤትህ ጋር ሲያፋጥጥህ ደርሰህ አባት ሆኜ ልቆጣጠር ልትል ነው?

‹‹ምን እያወራሽ ነው? መቼስ ቢሆን ልጄን መቆጣጠር መብት የለኝም?››

‹‹አላልኩም! ልጅህን መቆጣጠር መብትህ ነው፤ … ግን ጊዜ ሰጥተህ የማትጨነቅላትን ልጅ ዛሬ ደርሰህ የት አመሸች ስትል ምን ሳርግ››

‹‹በጣም ጥሩ ልጅቷን አንዘላዝለሻታል ማለት ነው፤ … ሰዓቱ ስንት ነው? … እስቲ ተመልከች አንዲት አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላት የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪ እንዴት ነው እስከ ሁለት ሰዓት ተኩል የምታመሸው?›› አላት ነጠላዋን አስተካክላ መስቀልኛ በማድረግ እንደወትሮዋ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለስግደት የምትሄደው ሚስቱ ላይ እያፈጠጠ።

‹‹አመሸች እንግዲህ ምን ታደርገዋለህ … ከአባቷ የወረሰችው አንድ ነገር ቢኖር ይህ ነው። ገና ሕፃን ሳለች ጀምሮ በአግባቡ እንደ ወላጅ ቤቱ ገብቶ ያላጫወታት አባት፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር እንዲያድርባት ያላስተማራት አባት፣ እንኳን እሱዋን እራስን በእግዚአብሔር መንገድ ለማራመድ የማይጥር አባት ሲያጋጥማት የሚያመሽበት ጭለማ ናፍቋት ቤቱ አስጠላት … ምሽቱ ተመቻት!››

በቀልድ መሰል ንግግር የተጀመረው የባልና ሚስቱ ጨዋታ መጣፈጡን ረስቶ መረረ። ሚስት በልጅ አስተዳደግ በባል አለመታገዟ ሲያበሳጫት፣ ባል አባትነቱ ዋጋ እንዳጣ ሲያውቅ እጅግ ተበሳጨ። በተለያየ ፍላጎት ውስጥ ያደገችው ሜሮን ከልካይ ሳይኖራት ዘለለች። መዝለሏን ያወቀች እናት ብትታገላትም ማሸነፍ ስላልቻለች ተወቻት። ማምሸት ወንድ በር ድረስ ማምጣት ጀመረች። በአድራጎቷ ያዘኑ የሰፈሩ ሰዎች በትዝብት ከንፈራቸውን መጠጡ። የእናት የአባቷ ቤት በር ላይ የሰፈራቸው መተላለፊያ ላይ ይሉኝታዋን አውልቃ ጥላ ልጅነቷን ረስታ ተሳመች። ነጠላን ከንፈር ላይ አድርጎ አግድም ከማየት ውጪ ብልግናዋን ሊነግራት የደፈረ ጎረቤት ስለጠፋ በረታች። ለምክር ወንበር የሚስብ አባት፣ ከተጣመመችበት ለመመለስ የሚፈልግ አባት፣ አልፎ አልፎም ቀበቶውን ፈቶ የሚያስፈራራ አባት ስለሌላት እናቷን ናቀቻት። በጆሮዎቿ አድርጋ እንደምትሰማቸው ራፐሮች የእናቷን ንግግር ደነሰችበት።

‹‹ወይኔ እኔ አላውቅልህም መስዬ … ያለማቋረጥ ማምሸቴ ሳያንስ ጭራሽ ዛሬ ሳድር እናቴ ምን እንደምትል አላውቅም››

‹‹አቦ ባሉበት ይመቻቸው … አንዳንዴም የማደርን ነፃነት ይስጡና … ሁሌ ቀን ይሰለቻል … እንዲች ሾልካ የምትገኝ

ምሽትማ ታስፈልጋለች … ይልቅስ ሜሪዬ ፈታ በይ … ሻንጣ ውስጥ ያለውን ጀለቢያሽን አድርጊና ቤቱን ፏ አድርጊው››

‹‹ወይኔ ጉዴ … መስዬ ሙት ፈርቻለው … ለማንኛውም ሺሻ አለን? ሳንገዛ እኮ ነው የመጣነው››

የቅዱሳን ሥዕላት ሳይሆኑ ወጣትነት የሳባቸው የነጮቹ ፎቶዎች በአራቱም የቤቱ ግድግዳ አቅጣጫ ተሰቅለዋል፡፡ እነዚህን ወጣቶችን ለማማለል ሲሳሳሙ፣ ሩብ ጉዳይ እርቃናቸውን ሲላፉ፣ ቢች ዳር አሸዋ ላይ ሲንከባለሉ የሚታዩት ፈረንጆችን ለመምሰል የሳር ፍራሽ ላይ የሚንከባለሉ የሀገሬ ልጆች ብዙ ናቸው፡፡ ሜሮንም የሞቀ የእናትና የአባቷን ቤት ጥላ ፍቅረኛዋ መሳይ ለመቃሚያና ሺሻ ለማጨሻ የተከራያት ሕገ ወጥ ቤት ውስጥ ማደሯን መርጣለች፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክብር መዳሩ፣ በሥጋ ወደሙ መታተሙ ቀርቶባት ድንግልናዋ የተወሰደበት ሳር ፍራሽ ላይ ስትቅም መዋሏ ሳያንሳት ዛሬ ቃጢራ ልትቅም ወስናለች፡፡

በጎረምሳ ፍቀረኛዋ አባባይነት ማደሯን ስትወስን ጀለብየዋን ለብሳ ቤቱን አሞቀችው፡፡ ቡናው እየተቆላ፣ የገዙት ሳር ተጎዝጉዞ፣ ጫቱ ከኮባው ወጥቶ ዕጣኑ ጨሷል፡፡ የተወሰኑ ሰዎችን ብቻ የምታስተናግደው ቤት በጭሱ እፍን ብላለች፡፡ ሁሉን ጨራርሳ ቡናውን ለመቅዳት ስትሰናዳ በቀልድ መልክ ጓደኛዋን እያየች፡፡

‹‹ምርቃትህ ከዚህ የአሜሪካ እርዳታ ስንዴ ከመጣበት የማዳበሪያ ኮርኒስ ባያልፍም መርቅ›› አለችው፡፡ እጁን እያፍተለተለ እና እያፋጨ የተሰጠውን የመራቂነት እድል ለመጠቀም ያክል ጀመረ፡፡

‹‹ያረቢ አትበለን እምቢ … ቱቦ ቱቦ .. ቱቦ .. ሴሳ … ሳ .. ሳቱማ … ቱማ የሌ የሌ … በከቡሽ … ቡሽ”

‹‹ቡሽ ነገር ነህ … ከዚህ ውጪ ምንም ምርቃት እንደማታውቅ ታወቀብህ … እስቲ ይህ አሁን ምርቃት ነው እርግማን?››

‹‹እስቲ ዝም በይ ሜሪ … ዋናው ሐሳቡ ነው … ምርቃት ነው ብለሽ ካሰብሽ ይሆንልሻል” አላት በኮባ ተጠቅልሎ የተቀመጠውን ጫት እየፈታ

“ይልቅስ ልነዳው ነው?››

‹‹ንዳው!››

‹‹ያቺ ይህንን ምግብ የሆነ በርጫ ቃም ቃም አድርጊና ስትፈልጊ አሜሪካ ስትፈልጊ ገነት ግቢ … ብቻ እንጨቱን መጣልሽን እንዳትረሺ … አሜሪካም ሆነች ገነት የጫት እንጨት ይዞ መገኘት ያስጠይቃል››

ጫቱ ሲቃም ቡናው ሲጠጣ ሺሻው ሲሳብ ሰዓቱ ሄደ፡፡ በረባውም ባረባውም የምትስቀው ሜሮን አይኗ ቁልጭ አለ፡፡ በምርቃና የወረዛ ግንባሯን እያየ የሚያፈጠው መሳይ እንደገባላት ስሜቷ እንደተለወጠ ተረዳ፡፡ ደጋግሞ የሚነካካውን ሞባይል አሁንም አንሥቶ መልእክት ነገር ጻፈና ላከ፡፡ የምትሠራውን የምትናገረውን በአግባቡ የማታውቀው ሜሮን በተቀመጠችበት ተቁነጠነጠች፡፡ ደጋግማ የምትከተው ጫት አፍታም ሳይቆይ ውጣው ሌላ ለመውስድ እጇን ትሰዳለች፡፡

ሁኔታዋን እያየ በድል አድራጊነቱ የተደሰተው መሳይ ያጣመረውን እግሩን በተለያየ አቅጣጫ እየለቀቀ ያፍታታል፡፡ ውጥኑ የሰመረለት፣ ነግዶ ያተረፈ ነጋዴ፣ ዘርቶ የበቀለለት ገበሬ ይመስል ልቡን ይነፋል፡፡

ከወዲያ መልእክት የላከላቸው ጓዶቹ የግብዣው ጥሪ ደርሷቸው ከቤቱ ደረሱ፡፡ ተንኳኳ … ወትሮ ፈሪ የነበረችው ሜሮን ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ያቺ ጠባብ ክፍል ስትንኳኳ የሥጋ ቤት አምፖል የመሰለ ዐይኗን ሰደደች እንጂ አልፈራችም፡፡ መሳይ በዐይኑ ምልክት ሲሰጣት ልትከፍት ተነሣች፡፡ የተቀረቀረውን በር ስትከፍት የሦስት ጎረምሶች ዐይን ተሰካባት፡፡ ጥሪያቸው የራት ብፌ ነው እና መዘጋጀቱን ሲያውቁ ፍሪዳቸው ሜሮንን ተከትለው ገቡ፡፡ የጓደኛቸውን ግብዣ ሊቀበሉ፡፡ ጓደኛቸው መሳይም ከዚህ በፊት ያበሉትን የፍስክ ብፌ ውለታውን ሊከፍል በፈገግታ ተቀበላቸው፡፡

በአባቱዋ ያልተገራችው ወጣትም ለፍቅረኛዋ ጓደኞች መሥዋዕት ልትሆን ተሰናዳች፡፡ ኢትዮጵያዊነት ወግ ባልገባበት፣ ሃይማኖት፣ ምግባር ባላየው ሁኔታ፤ ባልገው ሊያባልጉዋት ወንድነታቸውን ፈተሹ፡፡ ከሰው የማይካፈሉትን ተካፈሉ፡፡ ሰዶማውያን በረከሱበት መንገድ ሊረክሱ ወጣትነታቸውን ሊያስረጁ ግብግብ ገጠሙ፡፡ የሀገሬ ሰዎች ፈጣሪያቸውን “አቤቱ ይቅር በለን” ብለው ጉልበታቸውን መሬት እያመላለሱ በሚጠይቁበት ወቅት እነሱ የራሳቸውን የእርኩሰት ዓለም ፈጥረው በጠባቡዋ ቤት ሰሚ የሌለው ጩኸት አሰሙ፡፡

# የነገዋ ቤተ ክርስቲያን

## ክፍል ሁለት

ዲ/ን ብርሃኑ አድማስ እንደሰበከው

***ውድ አንባብያን ባለፈው እትማችን ቤተ ክርስቲያን ማን ናት? የሚለውን መሠረታውዊ ዕውቀት መረዳት ይቻል ዘንድ ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ የሰበከውን ተከታታይ ጽሑፍ እንደምናቀርብ ቃል ገብተን የመጀመሪያውን ክፍል አቅርበንላችኋል። በመጀመሪያው ክፍልም የቤተ ክርስቲያንን ምንነት፣ የቤተ ክርስቲያን ባሕርያት አራት እንደሆኑ፣ ከእነዚህም መካከል ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት። የሚለውን ማቅረባችን ይታወሳል። በዚህ ወር እትማችን ድግሞ ከባለፈው የቀጠለውንና ሁለተኛውን የቤተ ክርስቲያን ባሕርይ "ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት" የሚለውን አቅርበንላችኋል። መልካም ንባብ፡-***

አንድ ሰው ስለ ቤተ ክርስቲያን ሲያስብ እንደ ፖለቲካ ፓርቲ አድርጎ ማሰብ የለበትም። በፖለቲከኞች ውስጥ አንድ የሚያደርግ ምንም የእግዚአብሔር መንፈስና ረቂቅ ኃይል የለም። ምድራዊና ጊዜያዊ ዓላማ፣ አሠራርና አስተሳሰብ ነው የሚያሰባስባቸው። በክርስትና ግን እንደዚህ አይደለም፤ በክርስትና ትልቁ ነገር ከእግዚአብሔር ጋራ አንድ መሆን ነው። አሁን ተመልከቱ ክርስቶስ ሳያድርብን ስለ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ነው እኛ መቆርቆር የምንችለው? አናስብ ማለት አይደለም ግን ሐሳባችንን እንኳን በየትኛው መንገድ ልናቀርብ እንደሚገባን እንድናውቅ ነው። አንድ ሰው ንስሐ ሳይገባ፣ ሳይቈርብ፣ እውነተኛ ሳይሆን፣ ክርስቶስ በእርሱ ሳያድር እንዴት ሆኖ ስለ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መናገር ይችላል? በጣም ከባድ ነው። በመናገራችን አንድነቱ የሚመጣ የሚመስላቸው ሰዎች አሉ፤ በመናገራችን ሳይኾን የክርስቶስ በመሆናችን ነው አንድነቱ የሚመጣው። በሁላችንም ክርስቶስ ከአደረ፥ የክርስቶስ ማደሪያ ከኾንን አንድ መሆናችን አይቀርም። አሁን ከክርስቶስ የተለየን ሽፍቶች ተጣልተን ምን አንድነት ልናመጣ እንችላለን? ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት በዚህ አንድነት ማመን አለብን። ክርስቶስ እንዳለው እርሱ በእኛ ማደር ይፈልጋል፤ ለሚያንኳኳው ጌታ የልባችንን በር ከፍተን ልናስገባው ያስፈልጋል።

በተለይ ከተሐድሶ (reformation)፣ ከ፲፮ኛው መቶ ክ/ዘመን፣ ከነሉተር መነሣት በኋላ በ፲ ሺዎች የሚቆጠሩ የእምነት ተቋማት ተቋቁመዋል። የእንትና ቤተ ክርስቲያን፣ የነእገሌ ቤተ ክርስቲያን የሚሉ በዝተዋል፤ ብዙዎቻችን አሁን የሚነሣብን ጥያቄ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ከኾነች ለምን እንዲህ ተከፋፈለች? የሚል ነው። በተጨማሪም ወይም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት የሚባል ተቋም፤ (WCC- World council of Churches) አለ። ይህን ተቋም በአብዛኛው የመሠረተው የፕሮቴስታንቱ (Protestant) ዓለም ነው። እነርሱ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት የሚለውን ሊክዱ ስለማይችሉ እንዴት ነው ታዲያ እንደዚህ ተከፋፍላችሁ አንድ ነን ልትሉ የምትችሉት? ተብለው ሲጠየቁ ምሁራኖቻቸው ምንድን ነው የሚሉት? በWCC አንድ ነን፤ ነው የሚሉት። እንደ እነሱ አባባል የወይን ግንዱ WCC ሆነ ማለት ነው። "ሁላችንም በክርስቶስ አምነናል በእዚያ እምነት ስንገናኝ በWCC አንድ እንኾናለን" ይላሉ። WCC የመጣ በ፳ኛው መቶ ክ/ዘመን ገና ፪፻ ዓመት እንኳን ያልሞላው ተቋም ነው። በዚህ አንድ ማኅበር አቋቁሞ እንዴት አንድ መሆን ይቻላል? ይህ ቀላል ጉዳይ አይደለም፤ ትልቁ የሃይማኖት ጥያቄ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ እምነት ካለ፣ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ከሆነች፣ እንዴት ነው ይህ ሁሉ ክፍልፋይ አንድ ሊሆን የሚችለው?

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስናጠና በዐፄ ዮሐንስ አንደኛ ዘመነ መንግሥት ቅባትና ጸጋ የሚባሉ ኑፋቄዎች ነበሩ። እነርሱም ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ያውኩ ስለ ነበረ ጉባኤ ተካሂዷል። የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አማናዊቱን ሃይማኖት መስክረው መናፍቃኑ ተረቱ። በዚህ ጉባኤ

አስገራሚው ክሥተት ቀባቶችና ጸጎች የተለያዩ ኾነው ሳለ በአንድ ሆነው አባቶቻችንን ሊከራከሩ መጡ:: በዚህ ጉባኤም የተዋሕዶው ሊቅ ሃይማኖት ስንት ናት? አላቸው:: እነሱም አንድ እንዳይሉ ሁለት ናቸው፤ ሁለት እንዳይሉ መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ይላል:: ጨነቃቸውና ዝም አሉ፤ ምን ያህል መሠረታዊ ጥያቄ እንደሆነ መመልከት ይገባል:: የቤተ ክርስቲያን አንድነት መሠረታዊ ጉዳይና የመናፍቃን ሁሉ መውጊያው ነጥብ ነው:: እግዚአብሔር ይህን እውነት ተረድተን እንድንኖር ይርዳን:: አሁን የፕሮቴስታንት አስተዋይ ምሁራን ይህን መሠረታዊ ጥያቄ መጠየቅ አለባቸው:: ሃይማኖት አንድ ነው፤ ጌታ እንዳለው መንጋው አንድ ነው፤ እረኛውም አንድ ነው:: ሌላ በረት የለም፤ በረቱም አንድ ነው:: የነእገሌ የሚባል በረት የለም፤ ሌላ በረት ያሉትንም አመጣቸዋለሁ ነው ያለው ጌታ::

ከአንድነት ሳንወጣ ሁለት ጥቅሶችን እናንሣ ይህ ቅርንጫፎቹን በተመለከተ በመኃልየ መኃልይ በምዕራፍ ፮፥፰-፲ "ስድሳ ንግሥታት፣ ሰማንያ ቁባቶች፣ ቍጥር የሌላቸው ቈነጃጅት አሉ፤ ርግቤ መደምደሚያዬም አንዲት ናት፤ ለእናትዋ አንዲት ናት፤ ለወለደቻትም የተመረጠች ናት፤ ቈነጃጅት አይተው አሞገሷት::" ይላል:: መኃልየ መኃልይ ከተለዩ የተለየ መዝሙር ነው፤ የተለየ ምስጋና ነው፤ የተለየ ምሥጢር ነው:: ይህ የተነገረው ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት ነው:: ርግቤ መደምደሚያዬም አንዲት ናት የሚላት ቤተ ክርስቲያንን ነው:: ቅዱስ ኢጲፋንዮስ በ፬ኛው መቶ ክ/ዘመን በእነቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ዘመን የነበረ የአሁንዋ ቆጵሮስ ሊቀ ጳጳስ ይህን አመስጥሮ እንዲህ ብሏል:: እነዚህ ፷ ንግሥታት ፹ ቁባቶች ቍጥር የሌላቸው ቈነጃጅት የተባሉት በክርስቶስ ስም የተከፈቱ ብዙ የሃይማኖት ድርጅቶች ናቸው:: በዚህ ዓለም ያሉ እነዚህና ወደፊት የሚከፈቱት ሁሉ የአንድ ወንድ ናቸው:: በሴተኛ አዳሪዎች መስሎ ማለት ነው፤ የሚያልፈው ወንድ ሁሉ እኔ ጋ ይገባል፤ እያሉ ተስፋ ያደርጋሉ፤ ልክ እንደዚሁ ሁሉ ክርስቶስ ያለው እኔ ጋር ነው፤ እኔ ጋር ነው፤ እያሉ ተስፋ ያደርጉታል::

ነገር ግን ለክርስቶስ ያለችው ሙሽራይቱ አንዲት ናት፤ እርሱ የሚያድርባት፤ የሚዋሐዳት፤ አካሉ የሆነችው፤ አንዲት ናት:: እርሷ ርግቤ፥ መደምደሚያዬ የተባለችው አንዲት ቤተ ክርስቲያን ናት:: ይህን በማነጻጸር ያመሠጠረውም በእርሱ ዘመን በሀገረ ስብከቱ መልስ የሰጠባቸው ፹ የሚሆኑ የሃይማኖት ድርጅቶች ስለነበሩባት ነው:: ይህ ቅዱስ አባት በ፬ኛው መ/ክ/ዘ እነዚህ ፹ ቁባቶች እነዚህ ናቸው ይላቸዋል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሯል ርግቤ አንዲት ናት፤ መደምደሚያዬ አንዲት ናት፤ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት፤ እኔም ከእርሷ ጋር ነኝ:: የእኔን ስም ስለ ጠራችሁ ብቻ፣ በእውነት ካልፈለጋችሁኝ ወደ እናንተ አልገባም፤ ብሎ በትንቢት አንቀጽ የተናገረበት ነው፤ ይላል::

እነዚህ ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ስም የተቋቋሙ እንደ ቁባት ያለፈውን ወንድ ሁሉ ተስፋ እንደሚያደርጉ ሴቶች ይቈጠራሉ:: በእውነት ምሥጢሩን ሳንረዳ 'ምን ችግር አለው? እዛም ወንጌል ነው፤ እዚህም ወንጌል ነው፤' ማለት አይገባም:: ስሙንማ አጋንንትም ይጠራሉ፤ በእርሱ የማያምኑ ደቂቀ አስቄዋ ስሙን ይጠሩ ነበረ፤ ተአምራትም ያደርጉ ነበረ:: ይህ ሁሉ ሰዎቹን የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አካል አያደርጋቸውም:: የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አካል የሚያደርገን ዋናው ክርስቶስ በእኛ አድሮ በአንዲት እምነት፣ በአንዲት ጥምቀት፣ በአንድ ሥጋ ወደሙ፣ ስንኖር ብቻ ነው:: በዚህ እንድንኖር እግዚአብሔር ይርዳን::

፪ኛው ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት፡- ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት የሚለው ብዙ ነገር የሚያስነሣ ነው:: "ሀበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ ወፈውሰነ በዝንቱ ጵርስፎራ ከመ ብከ ንሕየው፤ አቤቱ የአንተ በሆነ መንፈስ ቅዱስ አንድ እንድንሆን እርዳን፤ በዚህ በሥጋ እና በደምህ አድነን አንድ አድርገን ባንተ ሕያው እንኾን ዘንድ::" እያልን ነው የምንጸልየው:: ያለ ሥጋውና ደሙ አንድነት የለም፤ ሁልጊዜም የምንጸልየው በዚህ አንድነት ነው:: የምንጸልየውን በእውነት የምንሰማው ከሆነ ከላይ እንደተገለጸው በአባ ብንያም ታሪክ እንደተፈጸመው፣ ከእነዚህ ሁሉ ቅዱሳን ጋር

አንድ ሆነን እነአባ መቃርስ እንዳሉት፣ ሰማዕታቱ እነቅዱስ ጊዮርጊስ፣ እናታችን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ እነዚህ ሁሉ ቅዱሳን ባሉበት፣ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢራትን በሚፈጽምበት፣ ሁላችንን በሚባርክበት፣ በሚያነጻበት፣ አንድነት ውስጥ ነው የምንኖረው። አሁንም እግዚአብሔር ይህን አስተውለንና አክብረን እንድንጠቀም ይርዳን።

ስለ ቤተ ክርስቲያን ቅድስትነት ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን መልእክቱ ምዕራፍ ፭ ቁጥር ፳፭ ላይ በሰፊው ተንትኖልናል። ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት ሲባል ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ባል እና ሚስት በተናገረበት አንቀጹ ዘርዝሮ ሲናገር "እደውኒ ያፍቅሩ አንስትያሆሙ ከመ ክርስቶስ አፍቀራ ለቤተ ክርስቲያን ወመጠወ ርእሶ በእንቲአሃ፤" ባሎች ሚስቶቻቸውን በፍጹም ይውደዱ፤ እንዴት አድርገው ይውደዱ? ትለኝ እንደሆነ ክርስቶስ ቤተ ክርቲያንን እንደ ወደዳት ይውደዷቸው። ይልና ወረድ ብሎ "ቤተ ክርቲያን ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ስለ እርሷ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤" ይላል። ቤተ ክርስቲያን ምንም ነውር የለባትም። ይህ በጣም ታላቅ ነገር ነው፤ ከላይ እንደገለጽነው ቤተ ክርስቲያን የምድራውያንና የሰማያውያን አንድነት፥ የቅዱሳን ኅብረት ናት። ስለዚህ ቅድስና የሌለው ሰው ገብቶ አይሠራም። በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል። እናንተም በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ ነው የተባለው።

ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሲሠራ ልዩ ልዩ ድንጋዮች ይገባሉ፤ ዳሩ ግን ሳይስተካከሉ፣ ሳይጠረቡና ሳያምሩ በዘፈቀደ አይከመሩም። ለግንቡ በሚስማማ መልክ ተስተካክለው እንደሚቀርቡትና ያልተስተካከሉት ድንጋዮች ግንብ ውስጥ እንደማይገቡት ሁሉ ልክ እንዲሁ እኛ ምእመናንም የክርስቶስ አንድ ሕያው ቤተ መቅደስ ለመኾን በንስሓ፣ በምግባራተ ሠናያትና በተጋድሎ መስተካከል አለብን። በቅድስና፣ በነቢያትና በሐዋርያት ከሚሠራው የቅድስና መቅደስ ጋር አብረን ለመሠራት ያን መልክ መምሰል አለብን። የትኛውን መልክ? የቅዱሳንን መልክ፤ እሱ ምንድን ነው? ቅድስና፤ ያለ ቅድስና አንሠራም ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት ሲባል እንዲሁ ድንጋዩ ሁሉ ቅዱስ ነው ለማለት አይደለም። በዚያ የሚገኙ ግዑዛኑ ሁሉ ይባረካሉ፤ ቅድስናው ግን የእኛ የአማኞቹ ነው።

ስለዚህ አንድ ሰው የቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ ማለት የሚችለው በቅድስና ከቅዱሳን ጋር ኅብረት ሲኖረው ብቻ ነው። አንድ ቀላል ምሳሌ ላምጣና ላስረዳ የምንጠቀምበት ኮምፒውተር (Computer) ኔትዎርክድ (Networked) የሆኑ በገመድ ተገናኝተው የአንዱን መረጃ ሁሉም የሚያገኙበት አውታረ መረብ አላቸው። በዚህም መሠረት እዚያ ያለውን ኮምፒውተር እዚህ ያለው ኮምፒውተር ያውቀዋል፤ ያገኘዋል። ልክ እንደዛው በቅድስና ጉዞ ላይ ያለ አማኝ እንደዚያ ነው የሚሆነው። ምን ማለት ነው? የቅዱሳኑ ገንዘብ ሁሉ የኛ ይሆናል የኛ ገንዘብም የእነሱ ይሆናል። አንድ ነን፤ አንድ ላይ ተሳስረናል፤ ተያይዘናል፤ አሁን ከዛ በረከት ከወጣን ተቆርጠን ወድቀናል ማለት ነው። ከግንዱ ተቆርጣ የወደቀች ቅጠል ግንዱ ላይ ያሉ ቅጠሎች የሚያገኙትን ምግብ ልታገኝ አትችልም። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት ስንል የቅዱሳን አንድነት ናት ማለታችንም ነው። የሰበካ ጉባኤ አባል መሆን እንችላለን፤ የሰንበት ት/ቤት አባል መሆን እንችላለን፤ የሆነ ማኅበር አባል መሆን እንችላለን፤ የቤተ ክርስቲያን አባል ላንሆን ግን እንችላለን። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን የምትባለው የቅዱሳን አንድነት ናትና። ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ስለ ኾነች ቅድስና የሌላቸው፣ ንስሓ የማይገቡ ደንዳኖችና ኀጢአተኞች ሰዎች ከቅዱሳን ጋር አንድ ሆነው አይቆጠሩም፤ ሊቆጠሩም አይችሉም። እንዲህ ካልኾነ ግን ቅዱሳንን መስደብ፣ እግዚአብሔርንም መዝለፍ ነው።

ስለዚህ እኔ የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ የምንል ከሆነ ቅድስናችንን እንጠብቅ። እናመንዝር፣ አንስረቅ፣ አንዋሽ፣ ኃጢአትንም ሠርተን እንደኾነ ንስሓ እንግባ፤ ቅድስናው ሲኖረን ከቅዱሳን ጋራ ኅብረት ይኖረናል። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ማለት ተጋድሎዋቸውን ያልጨረሱ ምእመናንና ተጋድሎዋቸውን የጨረሱ ቅዱሳን አንድነት ናትና። ቅድስት ናት የምንላት ይህችን ነው፤ ይህን

አንድነት ነው ቅድስት የምንለው። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን ምን መሆን ይጠይቃል ማለት ነው? ቅድስና። መታወቂያና ሰርተፊኬት ብቻውን በቂ አይደለም፤ እርሱ በምድር ላይ ላለው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ይጠቅማል እንጂ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን የሚጠቅመው ቅድስና ነው። ለዚህ ነው ቤተ ክርስቲያን እኛን ለመቀደስ የምትደክመው። ቃለ እግዚአብሔር ታስተምረናለች፣ ታጸመናለች፣ ታሰግደናለች፣ ኃጠአታችንን እንድንናዘዝ ታደርጋለች፣ ተናዘዙ ትላለች፣ ከስህተታችሁ ታረሙ ትላለች፣ ቀኖና ትሰጠናለች፣ አለባበስ፥ አካሄድ አኗኗር፥ አስተካክሉ ትለናለች። እንቀደስ ዘንድ ታዘጋጀንና አባሎቿ ታደርገናለች።

አማኞችን የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አባላት ሳይኾኑ ሸንግለን ብንልካቸው ምንም ጥቅም የለውም። የባሰውን ፍርድ በመቀበል እንቀጣለን እንጂ፤ ተያይዞ መጥፋት ነው ትርፉ። ተሰብስበን ተምረን፣ ጸመን፣ ጸልየን፣ ሰግደን፣ መጽውተን፣ የሰበካ ጉባኤ አባል ብንኾን፣ አሥራት በኩራት አውጥተን ቅድስና ከሌለን ምን ዋጋ አለው? በአንድ በኩል እየገነባን በአንድ በኩል የምንንድ ከሆነ ምን ፋይዳ አለው? እነዚህን ነገሮች እየፈጸምን መልሰን በኃጢአት ከናድናቸው ምንም ትርጉም የለውም። ስለዚህ አንድ ሰው በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አምናለሁ ሲል ምን ማለቱ ነው? ያለ ቅድስና ከቅዱሳን አንድነት መጨመር እንደማይቻል አምናለሁ እያለ ነው። መቀደስ እንደሚያስፈለገኝ አምናለሁ፤ ያለ ቅድስና በባሕርይው ቅዱስ የሆነ ጌታዬ የወይኑ ግንድ ቅዱስ ስለ ኾነ ቅርንጫፉ እኔም ቅዱስ መኾን አለብኝ ማለቱ ነው። ቅዱስ ግንድ ላይ ርኩስ ቅርንጫፍና ፍሬ ሊኖር አይችልም፤ "ወእምፍሬሆሙ ተአምርዎሙ ይቀሥሙሁ እምአሥዋክ አስካለ፤ ወእምአሜከላ በለሰ፤ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፤ ከእሾህ ወይን፥ ከአሜከላም በለስ ይለቀማልን?" (ማቴ.፯፥፲፮) ያለው ለዚህ ነው። የእኛም ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት ስንል የቅዱሳን አንድነት ናት፤ ያለ ቅድስና ወደዚያ ማኅበር መቀላቀል አይቻልም፤ በመንፈስ አብሮ መሠራት አይቻልም። ተጋድሏቸውን ያልጨረሱ የሚለው ቃል የሚገልጸው ይህን ነው። ተጋድሏችን ምን ለመሆን ነው? ለመቀደስ ነው። ውጣ ውረዱ፣ ገዳም መሳለሙ፣ መጾሙ፣ መጸለዩ፣ መስገዱ፣ መታረቁ፣ የቀሙትን መመለሱ፣ የበደሉትን መካሱ፣ ይህ ሁሉ ለመቀደስና የቅዱሳንን አንድነት ገንዘብ ለማድረግ ማለትም የቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን ነው።

ለምሳሌ አሁን ከኛ መሐል አንድ ሰው ስለ ሠራው በጎ ሥራ የክብር ዶክትሬት ቢሰጠው በጣም ይደነቃል። ምክንያቱም ልክ ሳይማርና በዚያ የትምህርት ሥርዐት ሳያልፍ ከእነዚያ ጋር የሚተካከል ሥራ ስለ ሠራ ለዚያም ክብር ስለበቃ ነው የሚደነቀው። ወይም አሁን ከመካከላችን አንዱ አያድርግበትና ስለ ሠራው በጎ ሥራ ብላ አሜሪካ የምትባል ሀገር የክብር ዜግነት ሰጥቼዋለሁ ብትል ሰው ሁሉ እንኳን ደስ አለህ አይለውምን? እኛም የቅዱሳንን ዜግነት ለማግኘት ነው የምንደክመው። አንድ ሰው የአንዲት ምድራዊት ሀገር ዜግነት አገኘ ተብሎ እንኳን ደስ አለህ የሚባል ከሆነ፣ የቅዱሳንን ሀገር ዜግነት ማግኘት ምን ያህል ደስ ያሰኛል? ቤተ ክርስቲያንን፣ ምድራዊ ተቋሟን እንደ ኤምባሲ ልንወስዳት እንችላለን። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ የአሜሪካ ኤምባሲ የሚሠራው ለማን ነው? ለአሜሪካ ነው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም የምትሠራው ለሰማያዊው መንግሥት ነው። እዚያ ሀገር ስንሄድ ዜግነታችን ቅድስና ነው።

ስለዚህ ሰዎችን ታዘጋጅና (ታሠለጥንና)፣ ጾም ምስጋና ታለማምድና፣ የመላእክትን ሥራ፥ የቅዱሳንን ሥራ አለማምዳ፣ የቅዱሳንን ዜግነት ሰጥታ ወደ ሰማያዊት ሀገራቸው፣ ወደ ዋናው ሀገራቸው ትልካቸዋለች ማለት ነው። ዓላማዋ ይህ ነው፤ ጉባኤ የሚዘረጋው፣ አባቶች የሚያገለግሉት፣ የምትናዘዙት፣ መዝሙር የሚዘመረው፣ ቆመን የምንናገረው፣ ሌላ ምንም ዓላማ የለውም። ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት ሲባል በዋናነት ከእኛ የራቀ አንድን ሕንጻ፣ ገዳም፣ ቅዱስ ነው ብሎ ማመን አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት ማለት እኛ ራሳችን መቀደስ አለብን፤ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን አንድነት ናትና ወደዚያ ማኅበር መግባት አለብን፤ ሰማያዊውን ዜግነት ማግኘት አለብን፤ ወደዚያ የሚያሳልፈውን ቅድስና የሚባል ደብተርና

ፓስፖርት ወይም ቪዛ ከቤተ ክርስቲያን ማግኘት አለብን፤ ሥጋ ወደሙ የሚባል ማኅተም ማሳተም አለብን፤ ያን ጊዜ የእነርሱ አባል፣ ዜጋ ሆን ማለት ነው:: የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች በቤተ ክርስቲያን ማመን ማለት ይህችን አንዲትና ቅድስት ጉባኤ ፥ ይህን የቅዱሳን አንድነት በደንብ አድርጎ ማመን ማለት ነው:: ለዚህ ነው ቤተ ክርስቲያን ከእኛ ከስብስባችን በላይ ናት የምንል:: አሁን እኛ ስንሰበሰብ ቢያንስ የእያንዳንዳችን ጠባቂ መላእክት አሉ:: በቅዳሴያችን ጊዜ "ሠራዊተ መላእክቲሁ ለመድኃኔ ዓለም ይቀውሙ ቅድሜሁ ለመድኃኔ ዓለም፤ የመድኃኔ ዓለም ሠራዊት በፊቱ ይቆማሉ::" የመድኀኔ ዓለም ክርስቶስ ሥጋውና ደሙ ሲፈተት እሱ ራሱ ሲለውጥ፣ እሱ ራሱ ሲቀድስ፣ ሲያነጻ፣ መላእክት ይከባሉ:: እንደ አሸን ረግፈው (ወድቀው) ነው፤ አንዳንዶች እንደሚመስላቸው መላእክት አይረገጡም፤ መናፍስት ናቸውና በእግረ ሥጋ አይረገጡም:: ግን የሉም ማለት አይደለም፤ አሉ፤ ስላሉም ነው የምንጠራቸው::

ምስጋናችን፣ ቅዳሴያችን፣ ማሕሌታችን ሁሉ የሚናገረው ይህን አንድነት ነው:: ቅዱሳን የሌሉበት አንድነት ምን ያደርግልናል? ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት ማለት የእነዚህ የቅዱሳን ስብስብ ናት ማለት ነው:: እነዚያ ዛሬ መታሰቢያ የሚደረግላቸው ቅዱሳን አሉ:: ስማቸውን ስንጠራ በድርሳነ ሚካኤል ላይ ስታነቡ ተጠንቀቁ ይላል:: አንድ ቅዱስ ገድሉ፣ ድርሳኑ ወይም ተአምሩ ሲነበብ ራሱ ቅዱሱ መጥቶ ይቆማል፤ ድርሳኑ የእሱ ቃል፣ ታሪኩ የእሱ ታሪክ፣ ተአምሩም የእሱ ተአምር ነዋ! የእግዚአብሔር መንፈስ እኮ ከዚህ ከሞገዱ ይበልጣል፤ በዚህ በሞገዱ፣ በስልክ፣ በኢንተርኔት እንኳን እንገናኛለን:: እንኳን መንፈሰ እግዚአብሔር ሳይንሱ በፈጠረው ሞገዱም የተራራቀው መገናኘት ችሏል:: በእግዚአብሔር ጥበብ የበለጠ ነው የምንተሳሰረው:: ስለዚህ ከቅዱሳን ጋር አንድነት አለን:: በዚህ ዓለም ላይ በአውሮፕላን እንደምንሄደው ቅዱሳንም መጓጓዣ የሚያስፈልጋቸው አይደሉም::

ቅዱሳን በእግዚአብሔር ዘንድ የሠለጠኑ ናቸው፤ የሚያንጉዛቸው፥ የሚያመጣቸው፥ ከእኛ አንድነት የሚደምራቸው፥ በባሕርይው በሁሉ የመላው፣ ምሉዕ የሆነው እግዚአብሔር ነው:: እርሱ መንፈስ ነው፤ የሌለበት ቦታ የለም፤ የሚሳነው ነገር የለም፤ ከእኛ ጋር አንድነት አላቸው፤ ይህን ቅድስና ለማግኘት ስንጋደል ደስ ይላቸዋል:: በቅዱስ ወንጌል "እላችሃለሁ እንዲሁ ንስሓ ስለሚገባ ስለ አንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ደስታ ይሆናል::" (ሉቃ.፲፭፥፲) በማለት ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው እግዚአብሔርን ፈልገነው ወደዚህ ኅብረት ስንመጣ ይደሰታሉ:: ዛሬ ጠባቂ መላእክቶቻችን በእኛ ፍላጎትና ጥረት ደስ ይሰኛሉ:: እስከ መጨረሻው እነሱን ለማስደሰትና የቅዱሳን አንድነት ማለትም የቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን ያብቃን:: እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ እስከዚህ ሰዓት በቸርነቱ ጠብቆ በመግቦቱ ሳይለይ ቅዱስ የሆነ ቃሉን አንብበን እንድንጠቀምበት የቅዱሳን አምላክ አባታችን መድኃኒታችን አምላካችን እግዚአብሔር ይርዳን:: ስለ ቤተ ክርስቲያን ይህን ያህል እንድንገልጽ የረዳን አምላክ የተመሰገነ ይሁን:: ይቀጥላል...

**ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሲሠራ ልዩ ልዩ ድንጋዮች ይገባሉ፤ ዳሩ ግን ሳይስተካከሉ፣ ሳይጠረቡና ሳያምሩ በዘፈቀደ አይከመሩም:: ለግንቡ በሚስማማ መልክ ተስተካክለው እንደሚቀርቡትና ያልተስተካከሉት ድንጋዮች ግንብ ውስጥ እንደማይገቡት ሁሉ ልክ እንዲሁ እኛ ምእመናንም የክርስቶስ አንድ ሕያው ቤተ መቅደስ ለመኾን በንስሓ፣ በምግባራተ ሠናያትና በተጋድሎ መስተካከል አለብን::**